
# ማዕዶት




የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

ሚያዝያ ፲፱፻፸፯ ዓ. ም.

አዲስ አበባ

ቁጥር ፲፯

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

[illegible] ረታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

ሚያዝያ ፲፱፻፸፮ ዓ/ም

<u>አዲስ አበባ</u>

ቁጥር ፲፮

www.ethiopianorthodox.org

## ማዕዶት ፤

«ማዕዶት» የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜው መሸጋገሪያ ድልድይ ወይም መርከብ ማለት ነው ፤ ይህ መጽሔት በዚህ በሽግግር ወቅት በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነቷንና ሥርዓቷን ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ዜናዋንና ታሪኳን ልዕልናዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ «ማዕዶት» ተብሎ ተሰየመ ይህ መጽሔት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ እየተዘጋጀ በየአራት ወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ ይወጣል ።

ዋና አዘጋጅ ሊቀ ትጉሐን ገብረ ክርስቶስ ኃ/ ማርያም

ስልክ ቁጥር 110754

የፖ/ ሣ/ ቁጥር 1283

## ማውጫ ፤


| ተራ ቁጥር | አርእስት ፤ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፭—፮ |
| ፪ | የቅዱስነታቸው መልእክት | ፮— |
| ፫ | ፍፁም አለቃችንን እንከተል | ፰—፲ |
| ፬ | የሆሣዕና ተአምር | ፲—፲፪ |
| ፭ | ቀዳም ስዑርና አከፋፈሎት | ፲፪—፲፫ |
| ፮ | ትንሣኤ | ፲፫—፲፬ |
| ፯ | ማዕዶት | ፲፭— |
| ፰ | ርከበ ካህናት | ፲፮— |
| ፱ | የቅዱስነታቸው ጉብኝት ሀ/ በትግራይ ለ. በኤርትራ | ፲፯—፳፪ |
| ፲ | ቅዱስነታቸው ብፁዕ አቡነ ኢዮብን አነጋገሩ | ፳፪—፳፬ |
| ፲፩ | የዋና ሥራ አስኪያጁ ጉብኝት በፈረንሳይ | ፳፭—፳፯ |
| ፲፪ | ዋና ሥራ አስኪያጁ ለሥምሪት አራት መመሪያ ሰጡ | ፳፮—፳፰ |
| ፲፫ | ሰማዕቱ ቅ/ ጊዮርጊስ | ፳፱—፴ |
| ፲፬ | የእንጦጦ ኪ/ ምሕረት ታሪክ | ፴፩—፴፬ |
| ፲፭ | የመተሐራ ደ/ ሰላም መድኃኔ ዓለም | ፴፬—፴፰ |
| ፲፮ | ስለዱቤ ማሽን ከአባ ተስፋ ሞገስ የተደረገ ጥያቄና መልስ | ፴፰—፵፪ |
| ፲፯ | የአ. አ. አብ ክርስቲያናት በድርቅ ለተጎዱ የድንኳን ርዳታ አደረጉ | ፵— |
| ፲፰ | ለቅዱስነታቸው የተበረከተ መወድስና አማርኛ ቅኔ | ፵፫—፵፬ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

## ረሀብተኞችን እንርዳ

ጌታችን መድኒኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዘር በሙሉ ከዲያብሎስ ቁራኝ ከኃጢአት ዳኛ ለማላቀቅ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ ሙቼ ተቀብሬ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን መካከል ተነሥቼ አድንሃለሁ ብሎ በሰጠው ቃል መሠረት በየዘመኑ የነበሩት ነቢያት ስለልደቱ ስለሞቱና ስለትንሣኤው ሲተነብዩለት ከቆዩ በኋላ የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ከሕጻናት ጋርም በጥቂት በጥቂቱ አደገ በሠላሳ ዓመቱ ተጠምቆም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጹሞ ዲያብሎስ በሦስት አርእስተ ኃጣውእ ሊፈትነው ቢመጣ በትዕግሥት ድል አድርጎታል ።

ዲያብሎስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በልበ አይሁድ አድሮ እንደወንጀለኛ የሞት ፍርድ ቢያስፈርድበትም የመከራ ጽዋውን በትዕግሥትና በትሕትና ተቀብሎታል ። አይሁድ ይህ ሁሉ ተንኮልና ክፋት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሊፈጽሙ የቻሉ ራሳቸው በፈጠሩት ተንኰል ሳይሆን ዲያብሎስ በልባቸው አድሮ ስለሚያሠራቸው ነው ። ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስ ተንኩል መሆኑን ስለሚያውቅ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ሲል በመስቀል ላይ ሳለ የምሕረት ቃል አሰምቶአቸዋል ።

እግዚአብሔር አምላካችን ቀደም ሲል በአዳምና ሔዋን የተበደለው እርሱ ፣ በመስቀል ላይ እንደበደለኛ ተሰቅሎ የሞተውና የካሰው እርሱ ፤ አባታችን አዳም ይቅር በለኝ ብሎ መለመን ሲገባው በመስቀል ላይ ሆኖ ይቅር በላቸው ብሎ ወደአባቱ የለመነው እርሱ፣የርሱ ምሕረትና ቸርነት ምን ይረቅ? ምን ይደንቅ?ሊቃውንትም ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ዓለምን ያዳነበት ምሥጢሩ ይረቃል ብለው የተረኩት ስለዚህ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምና ዘሩ ከዘለዓለም ሞትና ሥቃይ ነጻ ለማውጣት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ፣ ሞትንም አሸንፎ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ሞትን እንዲያሸንፍ ለሰው ልጆች ሥልጣን ሰጥቶአል ። ነገር ግን ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱ ውለታ ሲውልላቸው እነርሱ የሚውሉለት ውለታ ምን ዓይነት ነው? ውለታውን ለመመለስ አንደኛ እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ኃይልህ ና በፍጹም ነፍስሕ ውደድ ሁለተኛ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ሲል ባለቤቱ ያዘዘውን ትእዛዛት መፈጸም ነው ።

እግዚአብሔርን እወዳለሁ ወንድሜን ግን አልወድም የሚል ካለ ተሳስቶአል ፤ ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን የማይወድ ሐሰተኛ ነው ፣ የሚያየው ወንድሙን ያልወደደ የማያየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወድ ይችላል? ብሎአል ።

ዓይነ ሕሊናችን ወደ ዓለም ሁኔታ ቢመለከት ከዘሩ ወደ ጽድቅ የምንመራበት ሥራ ለመሥራት ያስችለናል ። ዓለም በሮኬት በሐይድሮጅን በቦምብ በናፓል ፣ በኔትሮንና በመሳሰሉት የሰው ሕይወት ጸሮች ስትሰጋ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በእነዚህ በቅጽበት በሚያጠፉ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆን በሚያስቅቅ በረሀብና በቸነፈር ጭምር መሰቃየት ነው ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ከዘጠኝ ሚልዮን ያላነሰ ሕዝብ የዕለት ጉርስ አጥቶ በረሀብ አለንጋ ሲገረፍ ይታያል ። ለዚህ ሕዝብ ሕይወት ለማትረፍም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ያለውን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ የዓለም ሕዝብና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካላቸው ቀንሰው በመላክ የሚያሳዩት ትብብር እጅግ የሚያስመሰግን ነው ። ማንም ኢትዮጵያዊም ቢሆን ከግላዊና ከወርኃዊ ደመወዙ ፣ ከልብሱና ከቁሳቁሱ እየከፈለ ለመርዳት ፈቃደኛ ሆኖ ሲሰጥ ይታያል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ይህ ነፍስአድን ዘመቻ በቀለጠፈ ሁኔታ ቅስቀሳና የገንዘብ አስተዋፅኦም እያደረገች ነው ። የቤ/ክርስቲያናችን ርእስ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያም የወገኖቻችንን ሕይወት ለማትረፍና በቃለ ሕይወትም ምእመናን ልጆቻቸውን ለማጽናናት የገንዘብም ችሮታ ለማድረግ በየክፍላተ ሀገራቱ በተለይ በወሎና በትግራይም በኤርትራና በጎንደርያ ሉትን ረሀብ ያጠቃቸው ወገኖቻችን ርኀራኄ የተመላበትን አባታዊ በረከት በማድረስ ላይ ናቸው ።

ቅዱስነታቸው ድካሙኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በእነዚህ ክፍላተ ሀገራት እየተዘዋወሩ በረሀብ የተቸገሩትን ወገኖች በመጎብኘት በማጽናናትና የገንዘብ ችሮታ በማድረግ ዕርዛት ለደረሰባቸው ልብስ በመስጠት እንደ ማውታዎችም ወድቀው እንዳይቀሩ በትምህርት በዕውቀት እንዲያድጉና ለሀገር ሸክም ከመሆን ድነው ራሳቸውና ሀገራቸውን ለመርዳት ይችሉ ዘንድ በየአመችው ሥፍራ አዳሪ ት/ቤት እንዲሠራና በዚያውበ እንክብካቤ እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ያድጉ መመሪያና ትእዛዝ ለየሀገረ ስብከቱ በማስተላለፍ ሐዋርያነታቸውና የክርስቶስ እንደራሴነታቸውም እያስመሠከሩ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አሥኪያጅ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውም በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን በኩል በተጣለባቸው ከባድ አደራ መሠረት አባት እናት ላጡ ሕጻናትና በረሀብና በችግር ለሚሰቃዩ ወገኖችም የነፍስ አድን ርዳታ ለማግኘት በውጭው ዓለምና በሀገር ውስጥም ያለመሰልቸት እየተዘዋወሩ ርዳታውን በማሰባሰብ ላይ ይገኛሉ ። ድርቅ ባጠቃቸው ክፍላተ ሀገራት አሥራ ሰባት የመጠለያ ጣቢያዎች ለመክፈት የሚቻልበትም ጥናታዊ ቅየሳ በማድረግ ላይ ናቸው ።

ሁለቱ የቤ/ክርስቲያናችን መሪዎች «ባንተ ላይ ሊደረግ የማትፈልገውን ሁሉ በባልንጀራህ ላይ ሲፈጸም ለማየት አትሻ» የሚለውን ቃለ ወንጌል በተግባር ለመተርጐም በየክፍላተ ሀገራቱ አሥራሰባት የመረዳጃ ጣቢያዎች ተቋቁሞ ሊሰጥ ከተዘጋጀው የገንዘብ ፣ የእህልና የቁሳቁስ ርዳታ ሌላ አንድ ሚልዮን ብር እስኪሞላ ድረስ ለርዳታ ማቋቋሚያ ኮሚሽን በየጊዜያቱ በመስጠት ላይ ነው ።

በዚህ ወቅት ወገን ወዳድና በጎ አድራጊ ምእመን ሁሉ ለዚህ ለተቀደሰ ትሩፋት ከልብ መተባበር አስፈላጊ መሆኑን ሊረዳው ይገባል ። ወገኖቻችን ተወልደው ካደጉበት አድገው ከተዳሩበት ከተኳሉበትና ካጌጡበት ወልደው ከብደው ለወግ ለማዕርግ ከበቁበት ቀየአቸው ተነቅለው በማያውቁት ሥፍራ እንደሚገኙ የታመነ ነው ። እንዲያውም ከመባከንና ከመባዘን የተነሣ ቀኑ ሳምንቱና ወሩ ዘመኑና በዓላቱ የማይለዩበት ሁኔታም ገጥሞአቸው ይሆናል ።

ስለሆነም በችግር የተጐዱ ወገኖቻችን በወርኃ ትንሣኤ ቁራሽ እንጀራ ለመሻት በየቤታችን ሲመጡ በማግረርና በማንጓጠጥ ከማባረር ይልቅ የተቻለንን ያህል ርዳታ ብናደርግላቸው ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በትሩፋት አሸብርቆ ይኖራል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተርቤ አብልታችሁኛል ታርዤ አልብሳችሁኛል ። ታምሜ ጠይቃችሁኛል ። ያለውም ለወገኖቻችን የምናደርገውን ችሮታ መናገሩ ነው ። ስለዚህ አምላካችን እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጀልን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንድንበቃ ረሀብተኞች ወገኖቻችንን እንርዳ ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ትንሣኤ ምክንያት

በማድረግ በሬድዮ ፤ በተሌቪዥን ፣ በጋዜጣና በመጽሔቶች ለመላ ኢትዮጵያ

ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ሙሉ ቃል

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

በገጠርና በከተማ ያላችሁ ምእመናን ፣

በየሆስፒታሉም የምትገኙ ሕሙማን ፣

በመሐልና በየጠረፉ የቆማችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ መዋዕለ ጾሙን በደህና አስፈጽሞ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ ።

የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ። እርሱም አሁን ነው የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ ። (ዮሐ፡ ፭፳፭) በአለው መሠረት በመቃብር ያሉት ሁሉ አዳምና ሔዋን ከነልጆቻቸው ድምፁን ሰምተው ከሞት ወደ ሕይወት ከሐሣር ወደ ክብር ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገሩበት የነፃነታቸው ዕለት ነው ። የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ በሞቱ ሞትን ድል ነሥቶ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ብርሃነ መለኮቱን ገልጦ በሦስተኛው ቀን ተነሣ ።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ስለእኛ ኃጢአት ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በሦስተኛው ቀን ተነሣ ብሏል ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፭ ቁ ፡ ፫ ።)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በኵር ሆኖ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው በእርሱ ትንሣኤ የኛን ትንሣኤ ለማስረዳት ነው ።

ትንሣኤ በሁለት ይከፈላል አንደኛው ትንሣኤ ልቡና ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትንሣኤ ሥጋ ይሆናል ። ትንሣኤ ልቡና የምንለው በዚህ ዓለም ሳለን መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ሥራችንን ለመሥራትና ለመፈጸም በቅን ልቦና ተነሣሥተን ስንፍናን ከህሊናችን አስወግደን የምንሠራው ሥራ ሁሉ ትንሣኤ ልቡና ይባላል ። (ሮሜ ፡ ምዕራፍ ፲፫ ቁ ፡ ፲፩) ነቢዩ ዳዊትም ይትፌሣሕ እግዚአብሔር በተግባሩ ፣ እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይለዋል ።(መዝ፡ ፻፫ ፣ ፴፩) ሲል እንደተናገረው ሁላችንም የአምላክ ሥራ እንደመሆናችን መጠን በቅን ልቡና ተነሣሥተን በምንፈጽመው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ይደሰታል ።

ትንሣኤ ሥጋ የምንለው ደግሞ ሁላችንም በተስፋ የምንጠባበቀው በዕለተ ምፅአት የምንነሣው ትንሣኤ ነው ። የሰው ልጅ ሁሉ ሞቶ በመቃብር በስብሶ አይቀርም ሁሉም ከመቃብር ተነሥቶ በኵረ ትንሣኤ ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ መንግሥተ ሰማያትን ወርሶ የሚኖር ነው ። ተስፋ ማለት እንደማጉሊያ መነጽር ያለ ነው ። ማጉልያ መነጽር የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ እንደሚያሳይ ሁሉ ተስፋም በወዲያኛው ዓለም የምናገኘውን ክብር አጉልቶ አስፍቶ ያሣያል (ያስረዳል) ከዚህ ዓለም ወደ ሁለተኛው ዓለም የምንሸጋገረው በተስፋ ነው ።

በዚህ በትንሣኤ በዓል ዕለት ልናደርገው የሚገባን ቅዱስ ጳውሎስ ከህዋሳታችን አንዱ ቢታመም ሕዋሳት ሁሉ ከእርሱ ጋር ይታመማሉ ። አንዱ ደህና ሲሆን ሁሉ ደስ ይላቸዋል ። (፩ኛ ቆሮ ፲፪ ፣ ፳፭) ብሎ እንደ ተናገረው የወገኖቻችን ችግር የኛም ችግር ስለሆነ የነርሱም ማግኘትና መደሰት የኛ ደስታ በመሆኑ ሁላችንም በተቻለን መጠን መረዳዳት ይገባናል።የሰላም ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓሉን የደስታና የምህረት በዓል ያድርግልን ። ለዓለምም ሁሉ ሰላምና ረድኤትን ይስጥልን ። አገራችንን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ፍጹም አለቃችንን እንከተለው

አለቃ ተብሎ ለተሰየመው ሁሉ ፍጹምነት አይሰጠውም ፍጹም የሚያሰኘው ታማኝና ትዕግሥተኛ እውነተኛ ፍርድን ገንዘብ አድርጎ በፍጹም ወንበር በተቀመጠ ጊዜየሰውን ፊት አይቶ የማያዳላ ፣ጉቦ የማይቀበል ፣መማለጃ የማይበላ ፤ በጊዜያዊ ጥቅም ሰውን ያላታለለ በአመጽ ገንዘብ ዓይነ ህሊናው ያልታወረ ራሱን ዝቅ አድርጎ ወንድሙን ያከበረ ፤ አይቻልም እንጂ የሚቻልስ ቢሆን ስለ ሰው ሕይወት ራሱን አሳልፍ ሰጥቶ በመሥዋዕትነት የብዙዎች ቤዛ መሆን ሲችል ነው ፍጹምነትን የሚያገኘው ከዚህ ትእዛዝ ውጭ የሆነ ግን ፍጹም ሊባል አይቻልም እንግዲያውስ እንዲሁ ከሆነ ታጥቀን ገሥግሠን ለመድረስ ብንችል የምንፈልገውና በውነት ልንከተለው የሚገባን ፍጹም አለቃችን መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ማወቅ ይጠቅማል አሁንም ከሱ በቀር ሌላ ፍጹም የለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንሩጽ በትግሥት በእንተ ተስፋነ ዘጽኑሀ ለነ ወንትልዎ ለፍጹም መልአክነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተአገሠ ኀፍረተ መስቀል

መከራውን በመታገስ ኹነን በሃይማኖት ተጠብቆልን ወዳለ ተስፋችን እንገሥግስ ስለኛ ብሎ መከራ መስቀልን ታግሦ የተቀበለውን ፍጹም አለቃችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተለው ብሎ አስተምሮናልና ። (ዕብ፡ ፲፪ ፣ ፩፫ ። ፩፻/ ቁር ፱ ፣፳፩—፳፯ ። ) ሐዋርያውም እንከተለው ያለው እንምሰለው አብነት እናድርገው ስለኛ የተቀበለውን ነገረ መስቀልን እናስብ ሲል ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጋቢት ፳፯ በጥንተ ስቅለቱ በዕለተ ዓርብ የተሰቀለውን መከራ ሕሊና አስቦ በአእምሮ ተመራምሮ አንደበት ተናግሮ በጽሑፍ አስፍሮ ወስኖ ቈጥሮ ለመናገር የሚችል የለም ምርት በስፍር እንጂ በቁጥር እንዳይገኝ መከራውም እንደዚያ የበዛ ነው ። (ኢሳ ፶፫ ፤ ፯—፰ ። )

ዮሐንስ አፈወርቅም በቅዳሴ የገለጸውን የመከራውን ብዛት በዕለተ ዓርብ ከ፫ ሰዓት እስከ ፱ ሰዓት የተፈጸመበት በደልና ግፍ ብንመለከተው በመጠኑ ሕሊናችንን ወደ መስቀሉ አንጻር ያደርሰናል ቸርነቱንም ያስታውሰናል እንዲህ በማለት ምክንያቱን ገልፆታል ሁሉን የፈጠረ እሱን ያዙት ሁሉን የሚገዛ እሱን አሠሩት፤ ሕያው የሚሆን የአብ ልጁን እሱን አሰቃዩት በብስጭት እየጎተቱ ወሰዱት በፍቅር ተከተላቸው በሚሸልተው ፊት ከሐሩር ከቁር የምድንበት ጠጉሬን የምትሸልቱኝ በምን እዳየ ነው እንደማይል በግ እየተከተላቸው ሄደ ። ሊቃነ መላእክት እየራዱ እየፈሩ ከፊቱ የሚቆሙለት እሱን በአደባባይ አቆሙት ኃጢአት የሚያስተሰርይ እሱን ኃጥእ ነህ አሉት መኳንንቱን በሚገዛ በሱ ይሞት በቃ ፈረዱበት ለሱራፌል ጸጋውን እንደዘውድ በሚደፋላቸው በሱ የሾህ ዘውድ ደፉበት ለኪሩቤል ግርማውን እንደልብስ የሚያለብሳቸው እርሱን ለመዘበት ቀይ ግምጃ አለበሱት ኪሩቤል በክንፋቸው ተሸፍነው ከፊቱ የሚሠወሩለት እሱን አንድ አይሁዳዊ ፊቱን ደፋው በጥፊ መታው ።

የመላእክት ሠራዊት እየደነገጡ በሚሰግዱለት በሱ እየዘበቱበት ከፊቱ ተንበረከኩ እንዲህያለ ትሕትና እንደ ምን ያለ ትሕትና ነው ፤ እንዲህ ያለ ትዕግሥት እንደምን ያለ ትዕግሥት ነው ።

ይህን ያህል ዝምታ እንደምን ያለ ዝምታ ነው ይህን ያህል ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው ይህን ያህል ሰውን መውደድ እንደምን ያለ ፍቅር ነው የሰው ፍቅር የአብ የባሕርይ ልጁን ከዙፋኑ ስቦ አወረደው እስከሞት አደረሰው ኃጢአት የሌለበት ጌታን ኀጥእ ብለው ሰቀሉት ደጎንነት የሚያድል እሱን ከሁለት ወንበዶች ጋራ ቈጠሩት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ከጲላጦስ አደባባይ በክርስቶስ ላይ የተፈጸመውን በደልና ግፍ መገፈፍና መገረፍ በመጽሐፈ መስቀል መለስ ብሎ ስላየው ይህንን አስቃቂ ኀዘን በለቅሶና በዋይታ ለምእመናን ገልፆታል ።

ወደ ወንጌላውያን እነጋገር ተመልሰን ስንመለከተው ጲላጦስም ፈቃዳቸውን ይፈጽምላቸው ዘንድ የገረፈውን ራርተው ይተውታል አይሰቅሉትም ብሎ ነበር አይሁድ ግን በሞት አስወግደው በመስቀል ከፊታችን አርቀው እያሉ ስለጮሁ እርሱም የጩኸቱን ብዛት ሰምቶ ከሮሙ ንጉሥ ከቄሣር ጋር ያጣሉኛል በማለት ስቀሉት ብሎ አሳልፎ ሰጣቸው መስቀሉንም አሸከመውት ከሊስቶስ ጥራ ወደ ቀራንዮ ወስደው ሰቀሉት ።

በሰቀሉትም ጊዜ ሰባት ተአምራት ታይተዋል በሰማይ ፀሐይ ጨልሟል ጨረቃ ደም ሁኗል ከዋክብት ረግፈዋል በምድር የቤተመቅደስ መጋረጃ ከሁለት ተከፍሏል



አዕባን ተፈትተዋል መቃብራት ተከፍተዋል ሙታን ተነሥተዋል ኢየሱስም ሰባቱን መከራተ መስቀል ተናግሮ ሲጨርስ ተጠማሁ እንግዲህ ሁሉም ተፈጸመ ብሎ ራሱን ዘንበል አደረገና በፈቃዱ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው ለይቶ ለአዳም የሰጠውን ተስፋ ፈጸመለት ማለት ከመከራው



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል እንደተሰቀለ

አዳነው ከሲኦል አወጣው የአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ቀጠሮ በዚያች ሰዓት ውሳኔውን አገኘ ።

መቼም ቢሆን አይሁድም ተምኔታቸው አል ተፈጸመላቸውም የነሱ ምኞት ክርስቶስን ገድለው በክርስቶስ ደም ከሮማውያን ጋር ተስማምተው በሰላም ለመኖር ነበር ነገር ግን በግፍ ያፈሰሱት ንጹሕ ደም እየፈረደባቸው ከሮማውያንም ሆነ በዙሪያቸው ካሉት አሕዛብ ሁሉ ሰላም ነሥቷቸው ከኢየሩሳሌም ወጥተው እየተሰደዱ ከልዕልናቸው እየተዋረዱ ያያቸው ሁሉ እስራኤል መባላቸው ቀርቶ እነዚያ ፈጣሪያቸውን የሰቀሉት አረማውያን መጡ እያሉ እየተዘባበተባቸው መጠላትን ውርደትን ፤ ክፉ ስምን ፤ አትርፈው ጸጸት እንደ እሳት እየበላቸው በባዕድ ሀገር እንደጨው ዘር ተበትነው ፥ ቀርተዋል ።

በኢየሩሳሌም የቀሩትንም አይሁድ በአርባ ዓመት ከጥጦስ ምርኮ አያይዞ አስደናቂ ታሪክ ገጥሟቸዋል ይኸውም ለክብር ሳይሆን ለውርደት ለሕይወት ያይደለ የሞት ሞት ነው ።

በጥጦስ ሠራዊት ተማርከው ብሔረ እስራኤልን ለቀው ብዙ ቀን ከተጓዙ በኋላ በወረደባቸው የጦር በረዶ ደክመው እንደቅጠል ረግፈው ስለ ነበረ ሮማውያን ጉባዔ ሠርተው ሮምን ታህል አገር የነዚህ የርጉማን አይሁድ ዐይናቸው ሊያያት እግራቸው ሊረግጣት አይገባም ብለው ብርቱ ብርቱዎችን ለጀግንነታቸው ማስመስከሪያ መር



www.ethiopianorthodox.org

ጠው አስቀርተው የከሱትን የደከሙትን አይሁድ ሠላሳ ሠላሳውን ለእያንዳንድ ብር ሽጠዋቸው ሂደዋል ይህም ታሪካዊ ፍርድ ሲፈጸምባቸው ይሁዳ ፈጣሪውን ለሠላሳ ብር በሸጠላቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለውን በሠላሳ ብር ገዛነው እያሉ ሲዘባበቱ ውለው ነበርና በዚያም አጸፋ ሠላሳውን ለአንዳንድ ብር እንዲሸጡ አድርጓል ፤ የታሪኩ መገኛ ምስተኛ ዜና አይሁድ የጻፈው ሕፁፃን ጥራዝ ምስት ገጽ አንድ ነው እንግዲህ ይህን ትምህርታዊ ጽሑፍ በምሥጢር ለማጠቃለል ይመች ዘንድ ወደመግቢያው ርእስ መመለስ ያስፈልጋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተከተሉ ብዙ ናቸው የተከታዮቹ ዝርዝር በዚህ ጠባብ መስመር ለመግለጽ ባይቻልም እንኳን ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስን ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስን ፤ ጳውሎስን በቂ ሁኖ በከታይነት ያጠቃለዋል ጴላጦስ በጥንት ስቅለት ስለአይሁድነዋ ንጉሥከሙ ንጉሣችሁ እነሆ ሁሉንም ቢላቸው አይሁድ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር ያለ ቄሣር ንጉሥ የለም በማለት የሮማውያንን ዙፋን ተማጽነውት ነበር ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኃላ ግን ጴጥሮስና ጳውሎስ ሮም ገብተው አጸፋውን ለመመለስ አልቦ ንጉሥ ዘእንበለ እግዚአብሔር አምላክ ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ያለ እግዚአብሔር አምላ ከሌላ ንጉሥ የለም ብለው የሮምን መንግሥት የሚያልፍ የሚጠፋ መሆኑን በግልጽ አስተምረው አሳምነው አሳዝብን ሁሉ አጥምቀው ይልቁንም ከኒሮን ቄሣር ቤተ መንግሥት ገብተው ንጉሣውያን ቤተሰብን በማጥመቃቸው ከድፍረት ተቈጠረባቸውና ጴጥሮስ በመስቀል ተሰቅሎ ጳውሎስ በሰይፍ ተከልሎ እንዲሞቱ ትእዛዝ ስለተሰጠ ይህንን ጽኑ የሞት ፍርድ ያለፍርኀት በግፍ አደባባይ ተቀብለውታል ።

ርእሰ ሕይወት ክርስቶስም እርሱ የሾህ አክሊሉ ተቀዳጅቶ ለተከታዮቹ የብርሃን አክሊል አቀዳጅቶአቸዋል ። ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት ቶለዉ አሰሮ ሐዋርያት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍለጋ ተከተሉ እያለች እስከ አጽናፈ ዓለም ምስክርነት ስትሰጥ ኑራለች እነርሱም ይህን ተጋድሎ ተከታይነታቸውን ገልጸውታል በሐዋርያት ጊዜ የነበረው እግዚአብሔርን መከተል ይህንንይመስል ነበር የዘመኑ ሐዋርያት እኛስ ክርስቶስ ለመምሰል በምእመናን መካከል የምናሳለው ተአምር ምንድን ነው ? በመድረክ ላይ ቁሞ በመስበክ በማስተማር ገጸ ንባብ በመደርደር ፤ወግና ምሳሌ በማነባበር ልበ ምእመናንን በማስመረር የጉባዔ ጊዜ በማስረዘምና በማሳጠር ነው ወይስ ሌላ መልክ አለው ይህ መሆን የለበትም ሊሆንም አይገባም ከኛ የሚጠበቅ ተአምር ቢኖር ሥርዓተ ጥምቀት ወቁርባን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ምን ያህል እንደተጠበቀ የመለኮትና የትስብዕት ተዋሕዶ ምሥጢር በካህናት ልቡና ምን ያህል እንደሆነ አውቀን ተረድተን ሥርዓቱ አልተጠበቀ እንደሆነ ለማስጠበቅ ምሥጢር ያልታወቀ እንደሆነ ለማሳወቅ ከሕይወት እስከ ሞት በሚያደርሰው ሐዋርያዊ ጉዞ ተጉዐን ለሰማዕትነት በሚበቃ ሥራ ተከታይነታችውን በማረጋገጥ ነው እንዲህ ካልሆነ በሐዋርያትነት ስም መጠራት የለም ከምእመናንም ተከታይ አናገኝም ከዚህም በላይ ቅዱስ ጴጥሮስ ፍለጋውን እንከተል ዘንድ ምልክትን ተወልን ያለውን ቃል ባለመጠበቃችን ቅጣት እንዳያገኘን ምልክቱን ጠብቀን ፍለጋውን ለመከተል በጥቃትና በትጋት መከታተል ይኖርብናል ። የጀመርሁትን ጹሑፍ በዚህመንፈሳዊ ምክ አጠቃልላለሁ ።

አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል ።

## የሆሣዕናው ተአምር

«ሆሣዕና» መሠረታዊ ትርጉሙ «አሁን አድን የማዳንህ ሥራ እኑኑ ይገለጥ » ማለት ነው ። በግዕዝም መድኃኒት ማለት ይሆናል ።

በዓለ ሆሣዕና የተጀመረውም አስቀድሞ በነቢዩ ዘካርያስ «የጽዮን ልጅ ሆይ ደስ ይበልሽ አንቺም የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ እነሆ ንጉሥሽ (ክርስቶስ) ጻድቅና አዳኝ ነው ትሑት ሆኖ በአህያና በወርንጭላይቱ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል ሠረገላን ከኤፍሬም የፈረሱንም ኃይል ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ የሰልፍም ቀስት ሁሉ ይሰበራል ለአሕዛብም ሰላምን ያውጃል ። ተብሎ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም የመጣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ የክብር አጀብ በመዝሙርና በእልልታ ወደ ቤተ መቅደስ በገባበት ዕለት ነው ።

ይኸውም የባሕርይ አምላክነቱን ክብር በፈቃዱ ዝቅ አድርጎ በአህያና በአህያይቱ ግልገል መቀመጡ ፍጹም ትሕትናውን ያመለክታል ።

በሌላም በኩል ዘመነ ሰላም መሆኑን ያበሥራል ፈረስና ሠረገላ የጦርነትን ዝግጅት የሚያመለክቱ ሲሆን ክርስቶስ ግን የሰላም ንጉሥ በመሆኑ በፈረስ ሠረገላ ተቀምጦ መታጀብን አልፈለገም ።

ፈረስና ሠረገላው ቀርቶ በአህያና በውርንጭላው ተቀምጦ መታየቱም እንኳ ከፍተኛ ድንጋጤን ፈጥሮ መላ ኢየሩሳሌም ታውካ እንደ ነበር ይታወሳል ። ከዚህም የተነሣ «ይህ ማን ነው? የሚል ጥያቄን አስከትሏል ። የተሰጠውም መልስ «ይህማ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው» የሚል ነበር። ታዲያ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ በመታጀብ ይህን ያህል ድንጋጤን ያስከተለ ይህ ንጉሠ ሰላም በፈረስ በሠረገላ ተቀምጦ በክብር አጀብ ሲያልፍ ቢታይስ ኖሮ የኢየሩሳሌም ኑዋሪ ሕዝብ ምን ያህል በተሸበረ ነበር? ።



በመሠረቱ ይህ ሁሉ ድንጋጤና መታወክ ሊፈጠር የቻለው የክርስቶስን ማንነት ካለማወቅ የተነሣ ነው ። ዛሬም ቢሆን ክርስቶስን የማያውቅ ትውልድ የመንፈስ ሰላም የለውም የሕይወትን መረጋጋት የሚሰጥ እውነተኛው የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ በአህያይቱና በውርንጭላይቱ ጀርባ ላይ ሳይሆን በየአንዳንድ ምእመን ልብ እንዲቀመጥበት ያስፈልጋል ያን ጊዜም ፍጹም የመንፈስ ሰላምና መጽናናት ያገኛል ስለዚህ ነበር ሐዋርያ ጳውሎስ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ ሲል መልካም ተምኔቱን የገለጠ ።

ክርስቶስ በዕለተ ሆሣዕና በአህያይቱ ግልገል ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ በገባበት ዕለት በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ተሠልፎ ያጀበው በነበረው ሕዝብ መካከል በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ። ሆሣዕና በአርያም እያሉ በመዝሙርየሚያመሰግኑ ሕጻናት ነበሩ ። ሕዝቡም ይህን ዝማሬ በማዳመጥ አጸፋውን በእልልታ ያስተጋባ

በዓለ ሆሣዕና እንኳንስ የሰው ዘር የቢታንያ ድንጋዮችም ሳይቀሩ በሰብአዊ አንደበት ለመዘመር የቻሉበት ዕለት ስለሆነ ከተመረጡት ታላላቅ ዕለታት አንዱ ነው ።

በሌላም በኩል ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱ የክብር አጀብ ለማሳየት ሳይሆን ለሥራም እንደነበር የሚያስረዳ ቤተ መቅደስን ከንግድ ሸቀጣ ሸቀጥ መጣያነት ወደፍጹም የጸሎት ቤትነት የመመለሱ ተግባር ነው ። ወገብረ መቅሠፍት ጥብጣቤ ዘሀብል የቃጫ ጅራፍ አብጅቶ በዚያ የሚሸጠውን የከብት መንጋ ሁሉ ካስወጣ በኋላ ርግቦች ነጻ እንዲለቀቁ አድርጓል ። የሸቃጮችንም ወንበርና ጠረጴዛ በመገለባበጥ ለምንዛሪ የቀረበውንም ገንዘብ ድብልቅልቅ እንዲወጣ ካደረገው በኋላ ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ ተጽፎ ነበር እናንተ ግን የሌባ ዋሻ የቀማኞች መሸሻ አደረጋችሁት በማለት ገሥጿቸዋል ።

ዛሬም የዚህ ዓይነት ድርጊት በአንዳንድ ታላላቅ አድባራት ዙሪያ ሲፈጸም መታየቱ ምሥጢር አይደለም ።



ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ አዕሩግና ሕፃናት እንደተቀበሉት

ነበር ። በዚህም ዝማሬ ያልተደሰቱ የኦሪቱ ካህናት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ብቻ ነበሩ ። ከነርሱም አንዳንዶቹ ወደ ክርስቶስ ቀረብ ብለው እነዚህ ልጆች የሚያቀርቡትን የምስጋና መዝሙር ትቀበለዋለህን? ሲሉ ጠየቁት እርሱም የሰጣቸው መልስ በልጆችና በሕጻናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ ተብሎ በዳዊት መዝሙር የተጻፈውን አላነበባችሁምን? እንግዲህ እነዚህ ልጆች ዝም ቢሉ እንኳ ድንጋዮች ሳይቀሩ ያመሰግናሉ የሚል ነበር ። ከዚህም የተነሣ ታዲያ እኮ ክርስቶስ ያን የቃጫ ጅራፍ እስኪያነሣ መጠበቅ አስፈላጊ አይመስለንም ። ስለዚህ እንደ ቁልቢ ገብርኤልና እንደ ዝቋላ አቦ እንደአህያ ፈጅ ቁስቋም ወዘተ ባሉት ገዳማት የሚፈጸም አሳፋሪ ድርጊት ሁሉ ተለውጦ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲሰፍንበት ማድረግ ይገባል ለዚህም መፍትሔው ይህ የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል በምልአት መስበክ ነው ። ወንጌል ያልተሰበከለት ሕዝብ የብዙ ዓይነት መጥፎ ልማድ ሁሉ ተገዢ ስለሚሆን



www.ethiopianorthodox.org

በተሳሳተ ሥእለትና ብዕዓት ከእግዚአብሔር የሚጠበቀው በረከት ወደ መርገም እንዳይለወጥ የበዓለ ሆሣዕናው ድንቅ ተአምር ትምህርት መውሰድ ይቻላል ።

በሌላ በኩል ቤተ መቅደስ የእያንዳንዱ ምእመን ሕይወትና የልብ ምሳሌ ስለሆነ ከዚያ አሪታዊ ቤተ መቅደስ ያን ሁሉ ሸቀጣ ሸቀጥ ያስወገደ የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ከእያንዳንዳችን ልብ የኃጢአትን ሸቀጥ አስወጥቶ የራሱን ሰላም ያሳድርብን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ። አሜን ።

መጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ
ም/ ኃላፊ ።

## ቀዳም ሥዑርና አክፍሎት

ቀዳም ሥዑር ማለት ምን ምን ባለመብላትና ባለመጠጣት በመጾም ብቻ የተሻረ ማለት ነው ።

እንግዲህ መብላት መጠጣት መክበር አለመብላት አለመጠጣት መሻር እንደሆነ ሲአስረዳ የተሻረ ቅዳሜ ተብሎአል ።

ምክንያቱም ከቀዳም ሥዑር በቀር በሁለቱ ሰንበታት ለማንም ክርስቲያናዊ መጾም እንደ ማይገባ በቅዱሳን ሐዋርያት መጽሐፈ ቀኖና ተመዝግቦ ይገኛል ።

ፋሲካ ዋዜማ በሆነው ሰንበት ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር ስለአደረበት እንዲጾም ሥርዓት ተሠርቶአል ። በመጾሙም የተሻረ ሲሉ መተርጉማን ቀዳም ሥዑር ብለውታል ።

በሌላ በኩልም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃዱ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በመስቀል ላይ ከለየ በኋላ ከዓርብ ፱ ሰዓት ጀምሮ እስከ እሁድ የሌሊት እኩሌታ በከርሠ መቃብር በቆየ ጊዜ ሐዋርያው ያዕቆብ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ ያለውን በማመን ትንሣኤውን ሳላይ እህል ውሀ አልቀምስም ብሎ አክፍሎት እሱ እንደ ጀመረ ይተረካል ።

ያዕቆብን መርህ በማድረግ ሐዋርያትም አክፍሎትን እንደፈጸሙ ታውቆአል ። ከዚያም በኋላ የእነሱን መልካም ምሳሌና አርአያ በመከተል ከካህናትና ከምእመናን የሚቻላቸው ዓርብና ቅዳሜን ሁለቱን ቀን የሚአክፍሉ ሆነዋል ።

የማይችል ግን አንዱን ቀን ማለት ቀዳም ሥዑርን ብቻ አክፍለው ቅዱስ ቁርባንን ይቀበላሉ ። ይህም ትሩፋት ስለሆነ የሚችሉትን አንዱን ቀን ብቻ ቢአክፍሉ የማያስነቀፋቸው መሆኑን ሳልገልጸው አላልፍም ።

አክፍሎት ማለትም ሲጾሙ ውሎ ሲጾሙ ማደርና ፈጽሞ ከእህልና ከውሃ መከልከል ነው ከዚያም በኋላ አስቀድሶ ቅዱስ ቁርባንን እንደሚቀበል ነው ።

እንግዲህ በዚህ ምክንያት ብዙዎች ክርስቲያኖች ድካም እየተሰማቸው ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሕይወታቸው እስከ ማለፍ የሚቃረቡ እንደአሉ ታውቆአል ።

ይህም የሚአስረዳ ክርስቶስ ለእነሱ ብሎ ስለ ሞተላቸው ይህነን አስደናቂ ውለታ እየአሰቡ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር በአደረ ጊዜ ከመብልዕ ከመጠጥ ተከልክለው ሕይወታቸውን ንጹሕ መሥዋዕት ስለአደረጉ የክርስቶስ መከራ መስቀል ተካፋይ መሆናቸው አያጠራጥርም ።

በሌላ በኩልም ሐዋርያት የአክፍሎት ጾም እንዲጾሙ የተደረገ እንዲያው ሳይሆን የክርስቶስ ትእዛዝ ይገኝበታል ይህንም የሚአስረዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሙሽራ ሚዜዎች ሙሽራው ከእሳቸው ጋራ ሳለ መጾም አይቻላቸውም ።

ግን ከእነሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል ያን ጊዜ ይጾማሉ ብሎ ነበረና።(ማቴዎስ ፱ ቁጥር ፲፭) እንግዲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት በሞት የተለየበትን ቀንና ሰዓት ዓርብ ከ፲፩ ሰዓት ጀምሮ እስከ እሁድ የሌሊት እኩሌታ እንደ ሆነ ተገልጦአል ።

ስለዚህ ሐዋርያት ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ጀምረው የአክፍሎት ጾም እንደ ጾሙ ታውቆአል ። በሌላ በኩልም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሕያው ሆኖ በመነሣቱ ለእኛም በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረቱን አጥፍቶልን ሙታን በትንሣኤ ዘጉባኤ በሚነሡ ጊዜ ከአካላቸው ምንም ጉድለት ሳያገኛቸው በሕያውነት እንደሚነሡ አስረድቶናል ።

ከዚህም ሌላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ በከርሠ መቃብር እስከ አደረበት ወቅት የአምላክነቱን ሥራ ከመሥራት እንደ አላቋረጠ ተመልክተናል ።



መለኮቱን ቦታ ስለማይወስነው ረቂቅ መለኮት ከነፍስም ከሥጋም እንደ አልተለየ ሲአስረዳ በሠርክ ዓርብ ማለት ፲፩ ሰዓት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በግዞት የነበሩ እስራኤል ዘነፍስን ከሲኦል አውጥቶ የነፍስ ነጻነት አውጆላቸዋል ።

መለኮት ከሥጋም እንደ አልተለየ ሲገልጥ ቅዳሜ ማታ ለእሁድ አጥቢያ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል መነሣቱን አውቀናል ።

በአንድ በኩልም ቀዳም ሥዑር በተባለው ቀን ካህናት የለመለመ ቄጠማ ይዘው ገብረ ሰላመ በስቀሉ የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ክርስቶስ በመስቀሉ ዓለምን የማዳኑን የምስራች ያበሥራሉ ።

ይህም ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን እንደ መሠረተና ዲያብሎስን ድል እንደነሣው የሚአስታውስ ነው ።

ከዚህም ሌላ የለመለመውን ቄጠማ የምሥራች መግለጫ ለምእመናኑ ያድላሉ ይህም እንዲያው ሳይሆን ምሳሌ ያለው ነው ። ቀድሞ በኖኅ ዘመን የላካት ርግብ ቈድለ ዕፀ ዘይት ይዛ የምሥራችን ለኖኅ እንደ አበሰረችው ይተረካል ።

ኖኅም ርግብን ከመርከብ ወደ ምድር የላካት ያለ ምክንያት አልነበረም ። የጥፋት ውሀ መጉደሉንና ምድርም በምን አኳኋን እንደምትገኝ ለመረዳት ስለ ነበረ ውሀው መጉደሉን አይታ በምድርም ልምላሜ እንደሚታይ ለማስረዳት ቈድለ ዕፀ ዘይት ይዛ በመመለስዋ ለኖኅ መስከረለች (ዘፍጥረት ፰ ቁጥር ፰፱) ካህናትም በቀዳም ሥዑር ይህነን ምሳሌ ይዘው ማየ ኃጢአት እንደ ደረቀና ማየ መርገም እንደ ጉደለ ለማስረዳት ቄጠማ ይዘው ልብሰ ተክሆኖ ለብሰው ዓለም የዳነበትን የክርስቶስን መስቀል ይዘው ለምእመናኑ የምስራች ይነግራሉ ዲያብሎስ ድል እንደ ተነሣ ዓለም እንደ ዳነ ይመሰክራሉ ።

ምንም እንኳ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ ቢታወቅም ሰማይና ምድር የማይወስኑት የባሕርይ አምላክ በጎቱም መቃብር ከአደረና ከዋለ በኋላ በሌሊቱ እሁድ የመለኮቱን ኃይል በትንሣኤ እስከ ገለጠ ድረስ ሐዋርያት ጥልቅ ኀዘን እንደተሰማቸው ታውቆአል ። ከእህልና ከውሀ ተከልክለው ትንሣኤውን ይጠባበቁ ነበረና

እንግዲህ እኛም የነፍስና የሥጋ ሕይወታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር ያደረበትንና የዋለበትን ዕለት ከመብልዕ ከመጠጥ ተከልክለን በኀዘንና በጸሎት ጸንተን ብርሃነ ትንሣኤውን መጠባበቅ ይገባናል ሕይወታችን እሱ ስለሆነ የትንሣኤውን በር ከፍቶልናልና ስለዚህ አክፍሎት እንደ ሚገባን በዚህ ትምህርት በመጠኑ ተገልጦአል ለዚህም ብርሃነ ትንሣኤውን ለማየት እግዚአብሔር ያብቃን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ ።

## ትንሣኤ ፤

ትንሣኤ ስንል ብዙ የሚያጠያይቀን ነገር ሊኖር ይችላል በመሠረቱ ግን ትንሣኤን በሁለት ልንከፍለው እንችላለን ይኸውም አንደኛው የሥጋ ትንሣኤ ሁለተኛው የሥጋም የነፍስም ትንሣኤ ነው የሥጋ ትንሣኤ ኤልያስ አንድ ምውት ኤልሳዕ ሁለት ምውት አሥነሥተዋል ።

እነዚህ ነቢያት ያስነሡአቸው ሰዎች የተነሡት የሥጋ ትንሣኤ ነው የሥጋ ትንሣኤ ስንልም ከዳግም ሞት የማያድን ትንሣኤ ነው ።

የሥጋና የነፍስ ትንሣኤ ግን ከዚህ የተለየ ነው ይኸውም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስየተገኘ ነው በርእሱ ትንሣኤ ብለን የተነሣነውም ስለዚሁ ታሪክ ለመተንተን ነው ።

ይህንንም ታሪክ ጌታችን በይበልጥ እኛን ለማሳወቅ ስለ ፈቀደ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ እያለ በቃል ያስተማረውን ትምህርት የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን የዕለት ሬሣ ወልደ መበለትን ወለተ ኢያኢሮስን ባስነሣ ጊዜ በአደረገው መለኮታዊ ኃይል ትንሣኤ መኖሩን ለዓለም ሁሉ አስታውቋል ።

እነዚሁ ሁሉ ለጊዜው ቢነሡም ተመልሰው ሙተዋል ዳግመኛም የሚአስነሣቸው ይሻሉ ስለዚህም ትንሣኤ ዘጉባኤን ይጠብቃሉ ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ሲያስረዳ በመቃብር የአሉቱ ሁሉ የክርስቶስን ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ በሕይወት ለመኖር ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ በሐሣር ለመኖር ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ ብሎ ተናግሯል ።

ከዚህም በኋላ በመጀመሪያ ራሱ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ከሙታን ተለይቶ እሁድ በመንፈቀ ሌሊት ተነሣ።ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ እምንዋም ወከመ ኃያል ወሕዳገ ወይን ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ እንዲል ።

ይህም ሲፈታ እግዚአብሔር ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ተነሣ የወይን ስካር እንዳለፈለት ሰው ያ ከእንቅልፉ ፈጥኖ እንዲነሣ ጌታም ፈጥኖ ተነሣ ወቀተለፀሮ በድኅሬሁ ለአዳምና ለሔዋን ከፈረደላቸው በኋላ በመስቀል ዲያብሎስን ድል ነሣው

ጌታም በሦስተኛው ቀን የተነሣበት ምክንያት አንደኛ በነቢያት አድሮ የናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ነው ትንቢቱም ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል በፊቱም በሕይወት እንኖራለን (ሆሴዕ ፭ ፣ ፫)



www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛም ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛ ኛው ቀን አነሣዋለሁ እያለ በምሳሌ የአስተማረውን በተግባር ለመፈጸም ነው ።

ሦስተኛ ለሰው ሦስት ጠላቶች አሉት እነርሱም ሞት፣ ኃጢአት ፤ ሰይጣን ናቸው እነርሱን ድል ነሥቶ እንደተነሣ

ለማጠየቅ ነው ። ይህም ሁሉ የሆነው በዕለተ እሁድ ነው በዚች በዕለተ እሁድ ለይኩን ብርሃን ብሎ በቃሉ ብርሃን ፈጠረባት በዚህም ምክንያት ዕለተ ብርሃን ትባላለችኋላም እሱ ተነሥቶ ብርሃኑ መለኮቱ ስለገለጸባት ነው ። በዚች ውም ቀን አይሁድን ከመፍራት የተነሣ ሐዋርያት ደጅ ዘግተው ተቀምጠው ሳሉ ጌታችን በዝግ ደጅ ገብቶ በፊታቸው ቁሞ ቸርአለቸሁን ሰላም ለሁላችሁ ይሁን አላቸው እነርሱም ምትሐት መስሎአቸው ፈሩ፡ጌታም አወቀባቸው ለምን ትጠራጠራላችሁ እጄን እግሬን አይታችሁ እመኑ አላቸው ። እነርሱም እጁን እግሩን ዳሰው ኋላም ሲበላ ሲጠጣ አይተው ትንሣኤውን አመኑ ተረዱ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለጌታ ትንሣኤ ሲመሰክር መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ ።

ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ ። አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም

ለሐዋርያት ሁሉ ታየ ከሁሉም በኋላ ከሁሉ ለማንስ ለእኔ ታየኝ ብሏል ። (፩ኛ ቆሮ ፲፭ ፫ ፣)

ይህም ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ የታየ መጀመሪያ ለመላእክት ቀጥሎ ለእነማርያም መግደላዊትከዚያም ለሐዋርያት መሆኑን ይገልጻል ።

ይህም ወርኀ ወርኃ ተሐድሶ ዕለቱም ዕለተ ድህነት ነው ሲሉ መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው ታይተዋል ። ስለሆነም ይህ ቀን (ዕለት )በጌታችን ትንሣኤ አማካይነት እኛም የዘለዓለም ትንሣኤና ክብር የምንቀበልበትት ስለሆነ ስናከብረው እንኖራለን ።

መ/ ይባቤ መልአክ



## ማ ዕ ዶ ት ።

ማዕዶት ማለት ዐደወ ተሻገረ ከሚለው ሥርወ ግሥ የወጣ ሲሆን ማዕዶት የሚለው ግዕዛዊ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎም መሻገር መሸጋገሪያ ድልድይ ማለት ነው ። ባሁኑ ጊዜ የምንገልጸው በዘመነ ሐዲስ ማዕዶት እያልን የምናከብረው ከምን የመጣ መሆኑንና በልማድ ወይም በልብ ወለድ እንዳይደለ ረጅም ታሪክና ሠፊ ምዕራፍ እንዳለው ለመግለጽ ነው የታሪኩ ወይም የባሕሉ አመጣጥ ቀደም ሲል ከዘመነ ኦሪት ሲያያዝ የመጣ እንጂ እንዲሁ በልማድ የመጣ አይደለም ።

ይኸውም የእሥራኤል ልጆች በረሀብ ምክንያት ከከነዓን ወደ ግብጽ ከወረዱ በኋላ በግብጻውያን ሥር ወድቀው ግፍንና በደልን እየተቀበሉ በከባድ አገዛዝ ተጨቁነውና ሰብአዊ መብታቸውን ተገፈው ለ፬፻፴ ዓመታት ያህል ሲኖሩ የርኅራኄ ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር ጭቆናቸውንና የደረሰባቸውንም ግፍ ተመልክቶ ሰፊውን የኤርትራን ባሕር ከሁለት ክፍሎ አሻግሮ አወርሳችኋለሁ ብሎ ተስፋ ወደ ሰጣቸው ምድረ ርስት እንዳሻገራቸው በዘጸአት ም- ፲፬፣ ፳፱ ላይ እንዲህ ሲል ይገልጸል የፈርኦን ሠራዊት አንድ ስንኳ ሳይቀር በባሕሩ ሲሰጥም የእስራኤል ልጆች ግን አንዳችም ነገር ሳይደርስባቸው በባሕሩ ውስጥ ሄዱ ውኃውም በቀኝና በግራ እንደ ግድግዳ ሆነላቸው ፣ ይላል ።

ስለዚህ በዘመነ ብሉይ የእሥራኤል ልጆች ከባርነት ወደ ነጻነት የተሻገሩበት ስለሆነ በዘመነ ሐዲስም ከዚህ ጋር አያይዘው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ከትንሣኤ ማግሥት ባለው ቀን እንዲከበር ያደረጉበት ዋና ምክንያት የመጀመሪያው ሰው በበደለው በደል በሠራውም ኃጢአት የሞት ሞት ተፈርዶበት ነበር ይህም በአዳም የተፈረደው ፍርድ እንደ ተላላፊ በሽታ ከአባት ወደ ልጅ እየተላለፈ ከሰው ልጅ ጋር ተቆራኝቶ ይኖር ነበር ነገር ግን በመስቀል ተሰቅየ አድንሃለሁ ሲል በሰጠው የደኅንነት ተስፋ መሠረት ሞት የማይገባው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን አፍስሶ ሕይወቱን ስለ ሰው ሕይወት ሰጥቶ ብዙ ጸዋትወ መከራንም ተቀብሎ በዲያብሎስ አገዛዝ ሥር የነበሩትን ነፍሳት ከሞት ወደ ሕይወት ከሲኦልም ወደ ገነት ያሸጋገረበት በመሆኑ ማዕዶት ተብሏል እሥራኤላውያን በፈርዖን ትእዛዝ ተፈጥሮን የሚያስጠላ መከራ ይደርስባቸው እንደ ነበር ሁሉ እንደዚሁም ከአዳም ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ተወልዶ እስከ ተሰቀለበት ድረስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ያህል ይሠቃዩ የነበሩት ነፍሳት እረፍታን ያገኙበት ዕለት ነው ።

እርግጥ ሰኞ ማዕዶት ነው ስንልን የኃጥአን ነፍሳት ከሲኦል የወጡት ሰኞ ሳይሆን ነፍሳት ከሲኦል የወጡት በዕለተ ዓርብ ነው ። ዓርብን በዓለ ነፍሳት ሰኞ የትንሣኤ ማግሥት እንዲከበር ሊቃውንቱ ወስነውታል ።

እንግዲህ እሥራኤላውያን በሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር አጋዥነት ሥጋዊ ነጻነታቸውን እንዳገኙ በዓመተ ዓለም የነበሩት ነፍሳትም በሲኦል ወድቀው በእግረ አጋንንት ተረግጠው ሲኖሩ ጌታ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ ወሐረ ኀበ እለ ሙቅሕታ ትነብር ነፍሶሙ ወሰበከ ሎሙ ግዕዛነ ፩ኛ ጴጥ ፫፣ ፲፰ አምስት ሺህከአምስት መቶ ዘመን ተግዘው ወደ ነበሩት ነፍሳት ሂዶ በእካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ እለ ውስተ ሲኦል ጸኡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሡቱ ወርእዩ ብርሃነ ዓቢየ ብሎ ግዕዛንን ሰበከላቸው ይላል በዚህ ጊዜ በሲኦል የነበሩት ነፍሳት ሁሉም ወጡ መንፈሳዊ ነጻነታቸውን አገኙ ተወሰዶባቸው የነበረው ልጅነትም ስለ ተመለሰላቸውና ክርስቶስ በደሙ ስላነጻቸው ነው ፤ ወንጌላዊው ዮሐንስም በደሙ እንዳነጻን አስመልክቶ ቃሉን ሲያብራራ (ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኲሉ ኃ ጣውኢነ)የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል ብሏል (፩ኛ ዮሐ መል ፩ ፣ ፯ ።)

ከዚህም የተነሣ በደሙ ታጥበን ከኃጢአታችን ስለነጻንና አምላካችን ክርስቶስ በወርቀ ደሙ ስለ ዋጀን የርስቱ ወራሾች ለመሆንም የበቃነውንና ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርነው በክርስቶስ ደም መሆኑን ማወቅና መገንዘብ የእኛ ፋንታ ነው የቤተ ክርስቲያናችንም ሊቅ አባ ሕርያቆስ እሥራኤላውያን ዘሥጋ ከግብጽ የግፍ አገዛዝ ተላቅቀው ወደ ምድረ ርስት ለመግባት የኤርትራን ባሕር ከሁለት ክፍሎ እንዳሻገራቸው እንደዚሁም እሥራኤል ዘነፍስንም ከሲኦል ወደ ገነት መሻገራቸውን አስታውሶ አማዕዶት ዘበኀቤኪ ዓደዉ አበው ቀደምት እሞት ውስተ ሕይወት ይላል ይኸውም ሲተረጎም የቀደሙ ሰዎች ከሞት ወደ ሕይወት ከፍዳና ከኀዘን ወደ ደስታ የተሻጋገሩብሽ ድልድይ አንች ነሽ በማለት እመቤታችን በማዕዶት (ድልድይ) መስሎ በሰፊው ጽፎ እናገኘዋለን ። ከዚህ ላይ ማዕዶት የሚለው ቃል ምን ያህል ምሥጢር ያዘለ መሆኑን እንገነዘባለን ።

እንግዲህ የቀድሞ ሰዎች በእምነታቸውና በመንፈሳዊ ሥራቸው ከማንኛውም የማዕበል ችግር ከኀዘን ወደ ደስታ ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ይሸጋገሩ እንደ ነበሩ ሁሉ እኛም ከሚደርስብን ችግርና ከሚፈታተነን ጠላት ለማምለጥ እምነታችን የጸና መንፈሳዊ ሥራችንም የተቃና ሁኖ መገኘት ይኖርበታል ።

ስለዚህ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ተመሰሉ ኪያየ ከመ አነ እትሜሰሎ ለክርስቶስ እኔ ክርስቶስን እንደመሰልሁ እናንተም እኔን ምሰሉ (፩ኛ ቆሮ ፲፩ ፣ ፩) ሲል እንደ ተናገረ እምነታችንን ድልድይ መንፈሳዊ ሥራችንንም መሰላል አድርገን ወደ እሱ እንቅረብ ከእሱ በቀር ሌላ ድልድይ የለንምና ።

ከነፈርግብ ግርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

## ርክበ ካህናት

ርክበ ካህናት ማለት ካህናት ተሰብስበው ስለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚመካከሩበትና ተመካክረውም ውሳኔ የሚያጸድቁበት ዕለት ማለት ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከፍዳና ከመርገም ነጻ ለማውጣት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ቀስ በቀስ እንደሰው ልጆች በማደግ በሠላሳ ዓመቱ ስለሰው ልጅ በደል ሲል ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ ነገር ግን ሞት ይዞ ሊያስቀረው አልቻለም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል ።

በሞቱም ሞትን ደምስሶ ለሰው ልጆች ነጻነቱን አጎናጽፎታል ። ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ እስከ አርባ ቀን ድረስ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጸ ሲታይ አንዳንድ ጊዜም በዝግ ቤት ካሉበት እየገባ ሲያስተምራቸውና ሲያጽናናቸው ከሙታንም መነሣቱን ለሚጠራጠሩ ምትሐት እንዳልሆነ ሲያስረዳቸው ቆይቷል ።

ከ፵ ቀን በኋላ ወደ ሰማያዊ ዙፋኑ ሲያርግ ፤ ከአሥር ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ሲነግራቸው እስከዚያው ሳይለያዩ ከአንድ ላይ መቆየት እንደሚገባቸው ነግሯቸው ነበር እነርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መሠረት በማድረግ በአንድነት ሆነው ሲጠባበቁ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው ።

መንፈስ ቅዱስም በወረደላቸው ጊዜ አንዲት ቋንቋ ብቻ ያውቁ የነበሩ ፸፪ ቋንቋ ተገልጾላቸው በየሀገሩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር ከብልየት ታደሱ ፍሩሃንና ድንጓጻን የነበሩ ደፋሮች ሆኑ የተሠወረው ምሥጢር ሁሉ ተገለጸላቸው ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ዕለቱ በስብከተ ወንጌል አልተሰማሩም ዓመት በዘኀብረት ከኢየሩሳሌም ከተማ ሳይወጡ ስለስብከተ ወንጌል ሥምሪት ሲመካከሩ ከቆዩ በኋላ ዓለሙን በመላ በ፲፪ ክልፍ መድበው ዕጻ በመጣጣል ተከፋፍለው ለስብከተ ወንጌል ተሠማርተዋል

ሐዋርያት ስብከተ ወንጌል ከጀመሩ በኋላ እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በማስተማር ተግባር ተሰልፈው ቢሠሩም እየተሰበሰቡ ስለ ስብከተ ወንጌል መመካከራቸውን አላቋረጡም ነበር ። በ፶፩ ዓመተ ምሕረት እንደገና በኢየሩሳሌም ከተማ ተሰብስበው ስለክርስትና እምነት መስፋፋት ተመካክረው እንደተለያዩ በዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ። የታወቀውን ጊዜ መጥቀሳችን እንጂ በየጊዜው እየተገናኙ ስለ ስብከተ ወንጌል መመካከራቸውን አቋርጠው አያውቁም ነበር ።

ከሐዋርያትም ቀጥለው ሊቃውንት በየጊዜው እየተሰበሰቡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሚደርሰው አንዳንድ ችግር ይወያዩ ነበር ። ከጊዜ በኋላ ካህናት በዓመት አንድ ቀን እየተሰበሰቡ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚመካከሩበት ዕለት ርክበ ካህናት የሚለውን ስያሜ አግኝቷል ቅዱስ ጴጥሮስም የበዓላትንና የአጽዋማትን ዕለታት በመጥቅዕና በዓበቅቴ እየተመራ እየዓርገ ንና ኢይወርድን ሲወስን ርክበ ካህናትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል በዋለ በ፳፭ ቀን እንዲታሰብ አድርጓል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም ይህንን መሠረት በማድረግ በዚሁ ዕለት እየተሰበሰበ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ይወያያል ይመካከራል አስፈላጊዎች የሆኑ መመሪያዎችንም ለምእመናን ያስተላልፋል ።

ይህ በዓል ካህናት ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ችግር እየተሰበሰቡ መወያየትና መመካከር እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው ችግር ሊወገድ የሚችለው ብቻ ለብቻ በመጋፈጥ ሳይሆን በመካከርና በመወያየት ስለሆነ ካህናት የሆኑ ሁሉ በአንድነት እየተሰበሰቡ በመመካከርና በመወያየት ቢሠሩ የቤተ ክርስቲያናችን ችግር ሁሉ በቀላሉ ሊወገድ እንደሚችል አንጠራጠርም ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



## ቅዱስነታቸው በትግራይ ክፍለ ሀገር ሐዋርያዊ ጉብኝት አደረ ጉ ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን ለማጽናናትና ለመርዳት በወሎ ፤ በትግራይና በኤርትራ ክፍላተ ሀገራት ሐዋርያዊና አባታዊ ጉብኝት አድርገዋል ስለጉብኝታቸውና ስለችሮታቸውም በወቅቱ በመገናኛ ዘዴዎች መገለጡ ይታወሳል ።



ቅዱስነታቸው የችግረኞችን መጠለያ ሲጐበኙ

ቅዱስነታቸው ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር በአየር ሲነሡ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤ ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ የቅዱስነታቸው ልዩ ጸሐፊ በቦሌ አእሮፕላን ጣቢያ ተገኝተው አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ። በዚሁም ወቅት ከቅዱስነታቸው ጋር አብረው የሄዱት ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ጸሐፊ እንዲሁም ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም የመንፈሳዊ አገግልሎት መምሪያ ም/ኃላፊ ናቸው ቅዱስነታቸው ከጥቂት ደቂቃ በረራ በኋላ ባሕር ዳር አእሮፕላን ማረፊያ ደርሰዋል ፤ በዚያም ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንኳን ደህና መጡ በማለት አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ባሕር ዳር አእሮፕላን ጣቢያ ለጥቂት ደቂቃ ቆይታ ካደረጉ በኋላ ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን በመቀጠል ጎንደር አዘዞ አእሮፕላን መረፊያ ሲደርሱ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ከሀገረ ስብከቱ ባለሥልጣኖች ጋር አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ከዚያም ወደ ትግራይ ክ/ሀገር በረራ በማድረግ መቀሌ አእሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጓድ ደስታ መሸሻ የክፍለ ሀገሩ ም/አስተዳዳሪ ጓድ ማሞ ብሒል የመቀሌ ከተማ አጠቃላይ ምክር ቤት ተጠሪ ጓድ ኃይሉ ገ/እግዚአብሔር የባሕልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪ ጓድ ነጋ በላይ የንግድ ሚኒስቴር ተጠሪ ጓድ ምንዳ ተፈራ የእርሻ ሰብል ተጠሪ በአእሮፕላን ጣቢያ ተገኝተው ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱና ከመንግሥት ባለ



www.ethiopianorthodox.org

ሥልጣናች ጋር በመሆን ወደ መቀሌ ጉዞ ቀጥለው በቅድስት ማርያም ቤተ/ክርስቲያን የሕሊና ጸሎት አድር ሰው በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተዋል ። ከዚያም የስምንቱ አድባራት አለቆችና ካህናት እንዲሁም የየሰን ብት ት/ቤቶች ተማሪዎች ምእመናንና ምእመናት እንኳን ደህና መጡልን በማለት ደስታቸውን በተለያየ ዝማሬ ገል ጸውላቸዋል ።

ከዚሁ የአቀባበል ሥነ ሥርዓት በኋላም ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስነታቸውን እንኳን በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ዋናጸሐፊ ግግር አድርገዋል ካደረጉት ንግግርም ውስጥ፤

ከልደተ ክርስቶስ ጀምሮ የክርስትና እምነት ብቻ ሳይሆን የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የተመ ሠረተው በዚሁ በትግራይ ነው ካሉ በኋላ ማንኛውም ኢትዮጵየዊ ጸሐፊ ቀለሙን በጥብጦ ብርዑን ቀርጾ የሚ ጀምረው በአክሱም እንደነበረ ገልጸዋል ። ስለጉብኝቱም ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል ።



ቅዱስነታቸው ችግረኞቹን ሲያጽናኑ

ደህና መጡ በማለት ንግግር አድርገዋል ። ከንግግራቸውም ውስጥ ፤

የቅዱስነትዎ ጉብኝት አያሌ ፍሬ ነገሮች የምንጠብቅ በት ከኀዘናችን የምንጽናናበት ችግራችንን የምናስወግድ በት አቋማችንን የምናጠናክርበት ታላቅ ኃይል ነው ብለን እናምንበታለን የሚል ይገኝበታል ።

ከዚህም በኋላ ሃያ የሚሆኑ ሊቃውንት ከቅዱስነታቸው ፊት ቀርበው ለቅዱስነታቸው ክብር የሚሆኑ አርባ ቅኔ ዎች አበርክተዋል ። ከዚህም በማያያዝ ብፁዕ አቡነ ገሪማ በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓት ርያርክ ዘኢትዮጵያ በታላቋ ታሪካዊት ክፍለ ሀገር የምትገኙ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ለሃይማኖታችሁ ቀናተኛ የሆናችሁ ካህናትና ምእመናን በዛሬው ዕለት የልዑል እግ ዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ በመካከላችሁ ስንገኝ ደስታም ኀዘ ንም ይሰማናል ይኸውም ከእናንተ መካከልበመገናኘታችን ደስታ የወገኖቻችን ችግር ሰናይ ደግሞ ኀዘን ይሰማናል ። ለሁሉም እግዚአብሔር በቅን ልቦና ብንለምነው ያለውን ችግር ሊያስወግድልን ይችላል በማለት አስገንዝበዋል ።



ቅዱስነታቸው ከዚህ በማያያዝ ሲናገሩ ባሁኑ ጊዜ በሰው በኩል የሚደረገው ርዳታ በቀላሉ የሚገመት አለ መሆኑን ጠቅሰው በመጽሐፍ ቅዱስ አሥር ለምጻሞች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዳዊት ልጅ ማረን ባሉት ጊዜ ወደካህናት ሄዳችሁ ሕይወታችሁን አስመርምሩ ሲል አዞአቸዋል ። የካህናት ኃላፊነት ሰውን ማገልገል እግዚ አብሔርን ማመስገንና ምእመናን ከእግዚአብሔር እንዳ ይርቁ ተግተው እንዲያስተምሩ አደራ ተጥሎባቸዋል ካሉ በኋላ ምእመናኑም የካህናትን ቃል ተቀብለው የተማሩትም ትምህርት ከጠበቁና ትእዛዙንም ከፈጸሙ የወረደውን ችግር ረሀብና ቸነፈር እግዚአብሔር ሊያስወግደው ይችላል ብለዋል ።

ቅዱስነታቸው አባታዊ ትምህርታቸውን ሲያጠቃ ልሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ችግር አቅሟ በሚፈቅደው መጠን ፈጥና የም ትደርስ መሆኑን አስታውቀው ትምህርትና መመሪያ ከሰጡ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው የአቀባበሉ ፕሮግራም በዚሁ ተጠቃልሎአል ።

በዚሁ ዕለት ከሰዓት በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በደብረ ሰላም ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ የሚገኘው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ ሥር የሚመራው ዕጓለ ማውታ የሚገኙበት አዳሪ ት/ቤትን ጐብኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት በመቀሌ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ካስቀደሱ በኋላ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመን ግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን በመቀሌ ከተማ አካ ባቢ የሚገኙትን የመጠለያ ጣቢያዎች ጉብኝተዋል በጣቢ ያው ሲደርሱም የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የጤና ጥበቃ ተጠሪዎችና የየድርጅቱ ኃላፊዎች አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በመጠለያ ላሉት ችግረኞች የሚያ ጽናና አባታዊ ምክርና መመሪያ ሰጥተዋቸዋል ። በዚሁ ሥፍራ ፭ የሚሆኑ የመጠለያ ጣቢያዎች ሲገኙ በነዚሁ መጠለያ ጣቢያዎች ላሉት ወገኖች መርጃ ይሆን ዘንድ ብር ፸፭ ሺህ (ሰባ አምስት ሺህ) ሲሰጡ ገንዘቡም በርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን በኩል እንደሚደርሳ ቸው ገልጸዋል ። በተበጨማሪም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ፲፯ የርዳታ ጣቢያዎች እንደምታቋቁምና በድርቅ የተጎዱ ወገኖችም ለመርዳት በከፍተኛ ዝግጅት እንደምትገኝ ቅዱስነታቸው አክለው አስታውቀዋል ።

ከዚሁ የጉብኝት ሥነ ሥርዓት በኋላም በክፍለ ሀገሩ ም/አስተዳዳሪ አማካይነት የመንግሥት ድርጅቶችን ጉብ ኝተው በኲሐ የሚገኙ በድርቅ የተጎዱ ወገኖችም እየተ ዘዋወሩ ከመጎብኘታቸውም በላይ አባታዊ ምክርና በረከ ታዊ ቡራኬ አድርገውላቸው ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ተመ ልሰዋል ።

ጎንደር አዘዞ አእሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱም ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሊቀ ሊቃውንት መንክር መኩንንና የቤተ ክህነቱ ሠራተኞች ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚያም ጉዞአቸውን በአእሮፕላን ቀጥለው ባሕርዳር አእሮፕላን ማረፊያ ሲደ ርሱ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊ/ጳጳስ የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች አቀባበል አድር ገውላቸዋል ።

ከዚያም በባሕር ዳር ሽምብጥ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው አስቀድሰዋል ። ከሰዓት በኋላ የአው ራጃው አስተዳዳሪ ጓድ ሻምበል ጌታቸው ወረደ በተገኙ በት ፳፱ እጓለ ማውታ የሚገኙበትን አዳሪ ት/ቤትን በብ ፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊ/ጳጳስ አማካ ኝነት አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል በዚሁም ወቅት ሕጻናቱ እንዳይራቡና እንዳይራቈቱ አደራ በማለት አባታዊ መመሪያ ሰጥተዋል ። ቀጥሎም ከባሕር ዳር ፺ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው ዓለም አቀፍ አእሮፕላን ማረፊ ያን በአውራጃው አስተዳዳሪ አማካይነት ጉብኝተዋል ። ከዚያም መልስ ፪፻፶ የቅኔ ተማሪዎች የሚገኙበት ት/ቤት ጉብኝተዋል ። ተማሪዎቹም ለቅዱስነታቸው ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔዎችን አበርክተውላቸዋል ። በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ት/ቤቱ በጥንቃቄ እንዲያዝና አስፈላጊውም ሁሉ እንዲሟላ ሀገረ ስብከቱን ከአደራ ጭምር አዘዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ጥር ፬ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ጀምሮ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካንና አዲስ የሚሠራ ውን ዘመናዊ የዘይት መጭመቂያ ሕንጻ በአውራጃው አስተዳዳሪ አስጎብኝነት ተመልክተዋል ። በዚሁ ዕለት ከሰዓት በኋላ በአእሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ።

ቅዱስነታቸው ቦሌ አእርርፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊ/ሥልጣናት ኤልያስ አበበ የቅዱስ ፓት ርያርክ ልዩ ጸሐፊ መጋቢ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ የመን ፈሳዊ አገልግዮት መምሪያ ኃላፊ እንኳን ደህና መጡ በማ ለት አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸውም አባ ታዊ ቡራኬ ሰጥተው እንዳበቁ ወደ መንበራቸው አምር ተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው በኤርትራ ሀ/ ስብከት ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉብኝት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ከጥር ፲፬ እስከ ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ድረስ በኤርትራ ሀገረ ስብከትና በአውራጃዎችዋ የሚያደርጉትን ሐዋርያዊ ጉብኝት ፈጽመው ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸው ይታወሳል ። ከቅዱስነታቸው ጋር ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ፤ ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ መጋቤ ካህናት መዓዛ ወልደ ኢየሱስ የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊና የየመምሪያው ኃላፊዎች በሥፍራው ተገኝተው አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር የአየር በረራ አድርገው በአሥመራ አራተኛ ዮሐንስ አእሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ጓድ ይስሐቅ ጸጋዬ የክፍለ ሀገሩ ም/አስ



ቅዱስነታቸው በኤርትራ ያሉትን ችግረኞች ለማጽናናት በሄዱበት ወቅት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር

ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ፤ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ም/ ኃላፊ አብረዋቸው መሄዳቸውም ተረጋግጦአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወደኤርትራ ሀገረ ስብከት ለመሄድ ቦሌ አእሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ ተዳዳሪ ጓድ አፈወርቅ ብርሃኑ የአሥመራ ከተማ ከንቲባ ሊቀ ትጉሐንሙሴ ዓለሙ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና የአሥመራ ከተማ ገዳማትና አድባራት አለቆችና አስተዳዳሪዎች ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከባለ ሥልጣኖች ጋር በአሥመራ ርእሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ የቤተ ክርስቲያኑ ደወል አስተጋብቷል ። በዚያ ተሰብስቦ የቅዱስነታቸውን መምጣት ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብና ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት የሰንበት ቅ/ቤት መዘምራን ሊቃውንት ደስታቸውን በጣዕመ ዝማሬ ገልጸውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸውም ሕዝቡን እየባረኩ ወደ ቤ/መቅደስ



ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ተገኝተው ስነ ትርኢቱን ተመልክተዋል ። ከዚህም በኋላ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አሥኪያጅ ሊ/ትጉሐን ሙሴ ዓለሙ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደህና መጡልን በማለት ንግግር አድርገዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊ/ጳጳስና የክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ ንግግር አድርገዋል ። ከንግግራቸው ውስጥ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ሐዋርያዊ ጉብኝት ለማድረግ የሄዱበትን ዋና ዓላማ ሲገልጹ በዜና ማሠራጫዎች እንደ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዚህ ዓለም መጥቻለሁ ሲል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ተናግሮአል ። ካለ በኋላ ቅዱስነታቸው መንፈሳዊና አባታዊ መልእክታቸውን በመቀጠል ሲያብራሩ ጨለማ ማለት ክፉ ነገር ነው የሰው ልጅ በኃጢአት እንዳይሰነካከል እውነተኛ ብርሃን የሆነውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ይኖርበታል ።

ይህ ችግር ይህ ድርቅ በእኛ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ አገሮችም እንዳለ ይነገራል ይሰማልም በአጠቃላይ በሰው ልጅ ላይ ልዩ ልዩ ፈተና ይደርሳል ፈተናውን ለማለፍ በጸሎት በምህላ እግዚአብሔርን በኅብረት ሆኖ መጠየቅ



ቅዱስነታቸው ከኅበኙአቸው የመጠለያ ጣቢያዎች አንዱ (አቆርዳት)

ሰማችሁት በሀገራችን በኢትዮጵያ በብዙዎቹ ክፍላተ ሀገራት በቂ ዝናም ባለመገኘቱ በግንቦት ወር ፲፱፻፹፮ ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር ተገኝተው ርዳታ አድርገዋል ። ካሉ በኋላ በዘንድሮውም ዓመት በዚሁ ክፍለ ሀገር ማለት በወሎ ባቲ በተባለው ሥፍራ ተገኝተው ችግረኞችን ጎብኝ ተው ርዳታ ማድረጋቸውን ሁላችሁም በሬድዮ እንደሰማ ችሁ ሁሉ በዚሁም ተመሳሳይ ጉብኝት ለማድረግ ነው የመጡት ብለዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩም«ሰላሜን እሰጣችለሁ በእኔ ያስፈልጋል ። እኛም በአንድነት በስምምነት ፈጣሪያችን ብንጠይቀው ሊሰማን ይችላል በማለት አባታዊ ምክራቸውን በቡራኬና በጸሎት ፈጽመው ወደተዘጋጀላቸው ማረፊያ ወደ መንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተመልሰዋል ። በአቆርዳትና በምጽዋም በዚሁ ተመሳሳይ ጉብኝት አድርገው ችግረኞችንም ጎብኝተው አጽናንተውና የገንዘብንም ርዳታ አድርገው ወደ አሥመራ ተመልሰዋል ።

በአሥመራ ከተማ ውስጥ ሀ/ የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክርስቲያንና ብዙ ሕሙማን የሚፈወሱበትን



www.ethiopianorthodox.org

ጠበል፤ ለ/ በመሠራት ላይ ያለውን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ቤተ ክርስቲያን፤ ሐ/ የመካነ ሰማዕት ቅ/ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ጐብኝተዋል ካህናቱና መዘምራኑ እንዲሁም የሰንበት ት/ቤቱ ተማሪዎችና ምእመናን ደስታቸውን ለቅዱስነታቸውገልጸውላቸዋል፡፡በመጨረሻም በፍኖተ ብርሃን አዳሪ ት/ቤት ጉብኝታቸውን አጠቃልለው ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፮ዓ/ምበአእሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ፡፡

ቦሌ ዓለም አቀፍ አእሮፕላን ጣቢያ እንደደረሱም ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊ/ሥልጣናት ኤልያስ አበበ የቅዱስነታቸው ልዩ ጸሐፊ መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊና ሌሎችም እንኳን ደህና መጡ በማለት አቀባበል ካደረጉላቸው በኋላ አእሮፕላን ጣቢያ ከ፰ ሺህ ብር በላይ ግምት ያለውን የርዳታ ዕቃዎችን እየተዘዋወሩ ጐብኝተው ወደ መንበረ ፓትርያርኩ አምርተዋል ፡፡

## ቅዱስ ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ኢዮብንና ተከታዮቻቸውን አነጋገሩ ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን ርዳታ ይዘው የመጡትን ብፁዕ አቡነ ኢዮብን የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳና ተከታዮቻቸውን የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋቸዋል ፡፡

በአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የጅቡቲ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ

ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ጸሐፊ

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅና ሌሎችም የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ተገኝተዋል ፡፡

በዚሁ ወቅት ብፁዕ አቡነ ኢዮብ ባደረጉት ንግግር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤ ቅዱስነትዎ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ሁለት ጊዜ በጎበኙበት ወቅት ተረድተዋል በታሪክም ቀደም ብሎ ቅዱስነትዎ ያውቀዋል በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ያለው ግንኙነት የጠነከረ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትን ችግር እንደሰማን የሩስያ ቤተ ክርስቲያን የተቻላትን ርዳታ በመጠየቅ የችግሩ ተከፋይ በመሆን የተገኘውን ርዳታ ይዘን መጥተናል ካሉ በኋላ ስለክርስትና ሕይወት አውስተው ሲናገሩ የክርስትስና ሕይወታችን አንዱ ለአንዱ የሚያዝንበት ዓላማችንን አውቀን ግዳጃችንን የምንፈጽምበት ሲሆን የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜን በላኩን መሠረት ርዳታውን አስረክበናል ብለዋል ፡፡

ብፁዕ አቡነ ኢዮብ ንግግራቸውን በመቀጠል የመጣንበት ዓላማ ርዳታውን ለማድረስ ቢሆንም ፓትርያርክ ፒሜን ለቅዱስነትዎ ያላቸውን ፍቅር የሚገይልጹ የቤተ ክርስቲያንን ምልክት የያዙ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ከደብዳቤ ጋር እንድናበረክት ስለላኩን ቅዱስነትዎ በትሕትና እንዲቀበሉን እንለምናለን በማልት ስጦታውን አበርክተዋል ፡፡

ብፁዕ አቡነ ኢዮብ ከዚያም አያይዘው ሲናገሩ ቅዱስነታቸው ከአሁን ቀደም ለሁለት ጊዜ ጉብኝት ማድረግዎ ቢታወስም በአሁኑ ዓመት የሩስያም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበትን የአንድ ሺህ ዓመት ኢዮቤልዩ ስለምታከብር በዚሁ በዓል ላይ እንዲገኙ ፓትርያርክ ፒሜን የላኳቸው መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

ሊቀ ዲያቆናት ብላድሜር በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር የሩሲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነታቸው የጠነከረ እንዲሆን በሁለቱም በኩል የነገረ መለኮትና የታሪክ ጉዞአቸው ከአሁን ቀደም ከሚደረገው የትምህርት አሰጣጥ በይበልጥ ታስቦበት ለዚህ ብቁ የሚሆኑ ሁሉ መሣተፍ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ባደረጉት የመልስ ንግግር የሩስያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምን ዓይነት እንደሆነ ሁለት ጊዜ መጥተን በጐበኘንበት ወቅት ተመልክተዋል ፡፡

በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን የሥራ ትብብር በተመለከትንበት ጊዜ በጣም ነው ደስ ያለን መንግሥትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ ተቀብለውናል ፡፡

በሔድንበትም ወቅት ገዳማቱንና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑትን እየተዘዋወርን ጎብኝተን ደስ ብሎን ተመልሰናል ብለዋል ፡፡

ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል የሁለት እኅት አብያተ ክርስቲያናት ትብብር በይበልጥ ዛሬ በጉልህ ታይቷል ለተጎዳ ወገኖቻችን ፈጥናችሁ በመድረስ ያደረጋችሁት ርዳታ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ፡፡

ከዚህም ሌላ ለመታሰቢያ የሚሆን ከፓትርያርክ ፒመን የተላከልንን ስጦታ በደስታ ተቀብለነዋል በበዓሉም ላይ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ለመገኘት ደስተኞች ነን በማለት ንግግራቸውን አጠቃለዋል ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በ፳፩ ፮/፲፱፻፸፯ ዓ/ም ከምሽቱ ፲፪፡ ከ፴ ለእንግዶቹ የራት ግብዣ አድርገዋል ፡፡



ቅዱስነታቸው ብፁዕ አቡነ ኢዮብን ባነጋገሩበትና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ባደረጉበት ወቅት

በግብዣው ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

የጠቅላይ ቤተክህነት የመምሪያኃላፊዎች ተገኝተዋል

የግብዣውም ፕሮግራም እንዳበቃ ቅዱስ ፓትርያርክ ለመጡት እንግዶችና ለፓትርያርክ ፒሜን የሚሰጥ ልዩ ልዩ ስጦታ አድርገውላቸዋል ፡፡

ስጦታውንም በተቀበሉበት ወቅት ብፁዕ አቡነ ኢዮብ ፤ ሊቀ ዲያቆናት ብላድሜር ባደረጉት ንግግር ስበታከፍተኛው ቅ/ጳውሎስ መንፈሳዊ ቅ/ቤት የተመለከትነው ሁሉ የቅዱስነትዎ አመራር ትክክለኛ መሆኑን ተረድተናል

በአንድ በኩል ችግረኞች ሲረዱና ትምህርት ሲማሩ ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክና የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲስፋፋ ት/ ቤት አቋቁሞ ከማስተማር የበለጠ ሥራ የለም የተመለከትነው በአቅራቢያ ያሉትን ነው በሌላ ቦታ ብንዘዋወር ብዙ ድርጅቶች እንዳሉ እናምናለን ብለዋል ፡፡

ከዚህም ሌላ በቅዱስነትዎ መልካም አመራር የሚሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ምን ዓይነት ትብብር እንዳላቸው የሚያስረዳ ነው ካሉ በኋላ ከቅዱስነትዎ የተበረከተውን ስጦታና የተመለከትነው የፍቅር ምልክት ስለሆነ ከልብ እናመሰግናለን ወደሀገራችንም በደረስንበት ጊዜ የተመለከትነው ሁሉ ትምህርት ስለሆነ ምስክርነታችንን ለሁሉም እናዳርሳለን በማለት ንግግራቸውን አጠቃለዋል ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በሰጡት የመልስ ንግግር «እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሆኖ የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ እንድንወያይ ስለአደረገ የተመሰገነ ይሁን በማለት ንግግራቸውን ጀምረው ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና በውስጧ ስለ አሉት ካህናት ሲናገሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት መሆኗን ማንም ያውቀዋል ፳ ሺህ አብያተ ክርስቲያናት ፤ ከ፪ መቶ ሺህ በላይ አገልጋዮች ካህናት አሏት ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ጽሑፍ ችሎታ መንፈሳዊ ሥራ በመፈጸም ሃይማኖት በመጠበቅ የኖረች እናት ቤተ ክርስቲያን ናት በአሁኑ ጊዜም መንግሥት በሰጣት መመሪያ በመጠቀም በ፰ ቦታዎች ከፍተኛ ት ቤቶች በ፲፬ ክፍላተ ሀገር ሰበካ ጉባኤ አቋቁማ መዋቅር ተዘርግቶ ለሁለት ጊዜ ያህል በእኛ ሊቀመንበርነት ስብሰባ ተደርጓል ሀገሪቷም ሆነች ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ባለቤት ናቸው ፡፡

የመልካም ታሪክ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ብዙሀብት ባይኖራትም ዳቦ አተታ አታውቅም በአሁኑ ጊዜ ድርቅ በአስከተለው ችግር ቤተ ክርስቲያኗ ቀደም ብላ ፰ ሺህ ሕጻናት በአሁኑ ጊዜ ፭ሺ፱፻ ችግረኞች ሕጻናት ተቀብላ ትረዳለች ለዚህ ሁሉ ችግር የሩስያ ቤተ ክርስቲያን ፈጥና በመድረሷ እናመሰግናለን ብለዋል ፡፡

ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው ግንኙነትና ወዳጅነት ተገልጿል ፡፡ ወዳጅነት ባለጊዜ በደስታ ጊዜ የሚደርስ አይደለም የመጨረሻ ወዳጅ የሚባለው በችግር ጊዜ አይዟችሁ ደርሰንላችኋል ስትሉ ችግሩ የተወገደልን መስሎናል ይህም በታሪክ ተመዝግቦ ይኖራል ለዚህም ልዑል እግዚአብሔር ብድራችሁን ይክፈላችሁ የሩስያና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በወዳጅነት ለዘለዓለም ጸንተው ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን በማለት አባታዊ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ፡፡

በመጨረሻም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ባደረጉት ንግግር እናንተ የሺህ ዓመት ኢዮቤልዩ ስታከብሩ የኢትዮጵያ





www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሁለት ሺህ ዓመት ኢዮቤልዩ ታከብራለች የሶብዩት ኅብረትና ኢትዮጵያ አን ድነታቸው የሚታወቀው ዛሬ ብቻ ሳይሆን ቀደም ያለ መሆኑን ታሪክ ያስረዳናል ኢትዮጵያዊ አብርሃ ወደ ሶብ የት ኅብረት ሔዶ ለመንግሥትና ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ሥራ እንደሠራ ታሪክ ያስረዳናል ።

በተለይ የአብርሃ የልጅ ልጅ ፑስኪንም ምን ዓይ ነት ሥራ እንደሠራ ሁሉም ያውቀዋል ሁለት አንባልም አንድነን ይህንን የአንድነት ክር የሚበጥስ የለም ።

በኢየሩሳሌም ያለንን ይዞታ ሌሎች የእኛ ነው ባሉን ጊዜ የምትረዳን እውነተኛ ምስክርነቷን የምትሰጠው የሩ ስያ ቤተ ክርስቲያን ናት ዛሬም ለችግረኞቹ መላክ ትችሉ ነበር ራሳችሁ መጥታችሁ ለችግራችን ተካፋዮች ስለሆና ችሁ ያላችሁን ፍቅር የሚገልጽ ነው ፍቅር የራሱ ቋንቋ አለው የእናንተን ቋንቋ ሁላችንም ብናውቅ እናንተም የእ ኛን ብታውቁ ምን ያህል ደስበአለን ነበር ምክንያቱም ቋንቋ ሁሉንም የሚያግባባ ስለሆነ ብዙ መወያየት ለብቻ መነጋገር ስለሚቻል ነው ብለዋል ዋና ሥራ አስኪያጅ ለወደፊቱም በማንኛውም ትብብራቸው እንደማይለዩን አስገንዝበው እንደበቁ በቅዱስ ፓትርያርኩ ቡራኬና ጸሎት የግብዣው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

ብፁዕ አቡነ ኢዮብና ተከታዮቻቸው በ፳፱/፩/፲፱፻፹፯ ዓ/ም ወደሀገራቸው ሲመለሱ

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ

ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊ ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህ ነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ

ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን የውጭ ግንኙነት ኃላፊ በቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ተገኝተው የወዳጅነ ነት አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።



## ዋና ሥራ አስኪያጁ በፈረንሣይ የሥራ ጉብኝት አድርገው ተመለሱ ።

በደረሰው ድርቅ ምክንያት አያሌ ኢትዮጵያው ያን በረሀብና በችግር መማቀቃቸው የታወቀ ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ድርጊት ዝም ብላ አላየችም ። ከመጀመሪያው ጀምሮ በሯን ከፍታ በችግር የወደቁትን ወገኖች በደጀ ሰላምና በመቃብር ቤቶች እየተ ቀበለች ልብስና ጉርስ በመስጠት ስትንከባከብ ኑራለች ። አሁንም የዚህ ምግባረ ሠናይ ክንውን በይበልጥ እንደቀ ጠለ ነው ።



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ከሚስተር ፍራንቸስኮ ኮሎምብ በፈረንሣይ የልዮ ከንቲባና ሴናተር ጋር ስለርዳታው ሲነጋገሩ

በተለይ ከ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ጀምሮ በረሀብ ምክንያት እናት አባታቸውን ያጡ ሕጻናትን ከልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር በማሰባሰብ በአሁኑ ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ከ፴ የሚበልጡ ቤተ ሕጻናት ከፍታ ከአምስት ሺህ ስልሳ ሕጻናት በላይ እየተንከባከበች በትምህርትና በዕውቀት እየኰተኰተች በማሳደግ ላይ ትገኛለች ።

ካለፈው ዓመት ጀምሮ በሀገራችን የደረሰው ችግር ከምን ጊዜውም የበለጠ መሆኑ በመገናኛ ዘዴዎች ተገል ጿል ። ይህን አሳሳቢ ሁኔታ በመመልከት የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስተዋሕዶቤተክርስቲያንከዓለምአብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ድርቅ ባጠቃቸው ክፍላተ ሀገር፲፯ የዕለት ዕርዳታ መስጫ ጣቢያዎች ለማቋቋም ጥናት አድርጋ ይህ ንን ፕሮግራም ለማካሄድ ፳፭ ሚሊዮን ዶላርና ፴፪ ሺህቶን እህል የሚያስፈልግ መሆኑ ዕቅድ ወጥቷል ።

እነዚህን ጣቢያዎች ለማካሄድ የተጠየቀው ገንዘብ አያሌ በመሆኑ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ ርዳታ ሰጭዎች በዚህ ፕሮግራም እንዲካፈሉ ጥሪ አስ ተላልፏል ። ጥሪውን ከተቀበሉ ድርጅቶች አንዱ በፈረንሳይ አገር የሚገኘው ሲማደ የተባለው ክርስቲያናዊ ድርጅት ነው ።

ሲማደ የተባለው ድርጅት ከዓለም አብያተ ክርስቲ ያናት የተላለፈለትን ጥሪ ከተቀበለ በኋላ ሁኔታውን በቦ ታው ተገኝተውየሚያስረዱልኡካን ከኢትዮጵያኦርቶዶክስ ተሕዋዶቤተክርስቲያን እንዲላኩለት ስለጠየቀ ሊቀ ማእም ራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስ ኪያጅና አቶ ሐዲስ ተረፈ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስደተኞች አገልግሎት ኃላፊከመጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፸፯ዓ/ም እስከ መጋቢት ፳፫ቀን ፲፱፻፸፯ዓ/ም በፈረንሳይ ሀገር ተገኝተው በኢትዮጵያ ስለደረሰው ችግርና የኢትዮጵያኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተክርስቲያንበድርቅየተጎ ዱትን ወገኖቻችን ለመርዳት የምታደርገውን ጥረትና ወደፊት ያላትን ፕሮግራም በፈረንሣይ ሀገር በሚገኙት የሕዝብ የመገናኛ ዘዴዎችና በልዩ ልዩ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት አስፈላጊውን ገለጻ ያደረጉ መሆናቸውን ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ጉብኝታቸውን ፈጽመው አዲ አበባ በገቡበት ወቅት በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል ።

በፈረንሳይ ሕዝብ ዘንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶቤተክርስቲያን በጥንታዊነቷ በታሪካዊነቷና በምታካሂ ደው ምግባረ ሠናይ ከፍተኛ ግምት ስለተሰጣት የተደረገ ላቸው አቀባበል አክብሮትና ፍቅር የተሞላበት እንደ ነበር ገልጸዋል ።

ፓሪስ ከተማ በቆዩበት ጊዜ በቴሌቭዥንና በሬድዮ ስለቤተ ክርስቲያናችን አቋምና ችግሩን በማስመልከት ስለምታደርገው እንቅስቃሴ መግለጫ እንዲሰጡ ሰፊ ዕድል ተሰጥቷቸው ልዩ ልዩ የመንግሥትና የሃይማኖት ጋዜጠኞች በተገኙበት ስለጉዞአቸው ዓላማ መግለጫ በማቅረባቸው የጉዞአቸው ዜና በዓለም በታወቁት የፈረን ሣይ ጋዜጦች ታትሞ የወጣ መሆኑን ጨርምረው ገልጸ ዋል ።

በፓሪስ ከተማ በቆዩበት ወቅት በልዩ ልዩ የሕዝብና የርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ስለ ቤተ ክርስቲያናችን የረጅም ዘመን ታሪክና በአሁኑ ወቅት በድርቅ የተጎዱትን ኢትዮጵያውያን ወገኖች ለመርዳት ዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚያስፈልጋት መሆኑን አስረድተናል ብለዋል ።

ሲማደ የተባለው ድርጅት ባወጣው ፕሮግራም መሠ ረት በፓሪስ የምናደርገውን የሥራ ጉብኝት ከጨረስን በኋላ ወደ ልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር ከተሞች በአውሮፕላን ፤



www.ethiopianorthodox.org

በባቡርና በመኪና እየተዘዋወርን ተመሳሳይ መግለጫ ሰጥተናል ። በዚህም መሠረት ስትራስ ቡርግ ፤ ኮልማር ፤ ቱሉዝ ፤ ማርሰይ ፤ ችሊዎ ፤ ናንት ፤ ግሮኖብል ፤ ሞፓልዮ ፤ ሞቤላርድና ቤል ሮረ የተባሉትን ከተሞች በጎበኙበት ወቅት ለየክፍለ ሀገሩ ጋዜጦች የሬድዮ ፕሮግራም ኃላፊዎች መግለጫ ስለምንሰጥ በየሄድንበት ቦታ ያስተላለፍነው መልእክት በሬድዮ ተላልፏል በጋዜጣ ታትሞ ወጥቷል ። በማለት አስረድተዋል ።

በፈረንሣይ ታላላቅ ከተሞች በተዘዋወርንበት ሁሉ የመንግሥትባለሥልጣኖችና የሃይማኖትመሪዎች በከፍተኛ አክብሮት እየተቀበሉ አነጋግረውናል ። አስፈላጊውንም ርዳታ ለማድረግ ቃል ገብተዋል ። በሕዝብ ስብሰባ ላይ ተገኝተን መግለጫ በምንሰጥበት ጊዜ ሀገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን በሚመለከት ጉዳይ አንዳንድ ጥያቄዎች ስለተነሡ ተጨባጩን ሁኔታ ለማስረዳት አመች ጊዜ አጋጥሞናል ብለዋል ።

በተባለው ከተማ የሚኖሩት የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ከልዩ ልዩ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር በመሆን በመንበረ ጵጵስናቸው በአክብሮት ተቀብለውን ስለሁለቱ እኅት አብያተ ክርስቲያናት ጥንታዊነትና አድነት ሰፊ መግለጫ አቅርበው ቤተ ክርስቲያናችን ለምታካሂደው ፕሮግራም አስፈላጊውን ርዳታ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው በፈረንሳይ ለሚኖሩ ሦስት መቶ ሺ አርመናውያን ክርስቲያኖች ርዳታ እንዲለግሡ ጥሪ የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ነግረውናል ።

የፈረንሳይ ሕዝብ ስለሀገራችንና ስለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ግምት አለው ። በአሁኑጊዜ በሀገራችን ስላለው ሁኔታ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አማካይነት የተዘበራረቀ ወሬ ስለሚሰማ እኛ በቦታው ተገኝተን ተጨባጭ መረጃ በመስጠታችን ብዙ ሕዝብ ተደስቷል ።

በኢትዮጵያ የደረሰው አሰቃቂ ዕልቂት በየጊዜው በቴሌቭዥን ስለሚታይና በጋዜጣ ስለሚታተም በኢትዮጵያውያን ችግረኞች ስም ኮፋዳ ይዞ ለልመና ያልተሰማራ መንፈሳዊና ሥጋዊ ድርጅት የለም በኢትዮጵያ ስም ባጅ በመሸጥ ዘፈን በማስቀረጽ ሙዳዩ ምጽዋት በማዞርና በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ብር እየተሰበሰበ ነው ። ነገር ግን ማዕከላዊ አሠራር ስለሌለው የተሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ ለችግረኞች ይዳረሳል ማለት ያስቸግራል ። አንዳንዶቹ ድርጅቶችም በኢትዮጵያ ስም የሰበሰቡትን ገንዘብ እስከ መቶ ስልሳ ድረስ ለራሳቸው መንደላቀቂያ አስቀርተው የተረፈውን እንደሚልኩ ከአካባቢው በሰበሰብነው መረጃ ለማወቅ ችለናል ።

በእኛ በኩል ሁኔታውን ካየን በኋላ በቤተ ክርስቲያን ስም የሚሰበሰበው ርዳታ በሰማይ አማካይነት በዓለም አብያተ ክርስቲላናት በኩል ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንዲላክ በለተስማማን ቢማደ የተባለው ድርጅት ከፈረንሳይ ሕዝብ የሚገኘውን የቆሳቁስና የጥሬ ገንዘብ ርዳታ ሰብስቦ ለመላክ ኃላፊነቱን ወስዷልብለዋል ።



ዋና ሥራ አስኪያጁ ከሚስተር ማርክ ብሩንሽቫይለር የሲማደ ዋና ጸሐፊና ከፓስተር ቤርናርድ ጋር ተገናኝተው ስለርዳታው ሲነጋገሩ

በአጠቃላይ በረፈንሳይ በቆየንበት ጊዜ ምንም እንኳ አየሩ ቀዝቃዛ ቢሆን ያገኘነው የሥራ ፍሬ ብዙ በመሆኑ የመንፈስ ሙቀት አልተለየንም ከሕዝብ ያገኘነው የሞራል ድጋፍ በጣም የሚያበረታታ ነው ። ድጋፍ የቃል ብቻ ሳይሆን ለተጎዱት ወገኖቻችን የሚደርስ በቂ የማቴሪያልና የገንዘብ ርዳታ በአስቸኳይ እንደሚደርስ ብዙዎቹ አረጋግጠውልናል ። በማለት ሊቀ ማእምራን አስረድተዋል ።

በመጨረሻም ወደ ጀኔባ ሄደው በፈረንሳይ ስለተደረገው የሥራ ጉብኝት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጽ/ቤት ባለሥልጣኖች ጋር ሰፊ ውይይት ያደረጉ መሆናቸውን በማስመልከት መግለጫቸውን ደምድመዋል ።

# ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ለሥምሪት ሥራ መመሪያ ሰጡ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን በቃለ አዋዲው መመሪያ መሠረት በየክፍላተ ሀገራቱ ሰበካ ጉባኤን ለማጠናከር ያመች ዘንድ ካሁን በፊት ሥምሪት አንድ ሁለትና ሦስት መካሄዱ በጋዜጦችና በመጽሔቶች ተገልጾአል ።

በዘንድሮው ዓመትም ሰበካ ጉባኤው ዕድገትና ጥንካሬ እንዲያስገኝለት በማለት በየሀገረ ስብከቱ የሥምሪት አራት ልኡካን ተሠማርተው ሰንብተዋል ። ለልኡካኑም ከየካቲት ፴እስከ መጋቢት ፪ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ድረስ በልማትናክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን አዳራሽ ሰሚናር ተሰጥቶአቸዋል። ሰሚናሩም በአቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ጸሎተ ቡራኬ የተከፈተ ሲሆን ከዚህም እያይዘው ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለ ሰሚናሩ ዓላማና ተግባር መመሪያ ሰጥተዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ ቤ/ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የቤ/ ክርስቲያናችን አለኝታ የሆነው ሰበካ ጉባኤ ከየት ተነሥቶ የት እንደደረሰ አንድ በአንድ ተንትነውለሰሚናሩ ተሳታፊዎች ካስረዱ በኋላ የዘንድሮው ሥምሪት አራት ተልእኮ ግን በፊት ይሰጥ ከነበረው ከሰበካ ጉባኤን መጠናከርያ ጋር አንገብጋቢና ነፍስ አንድ የሆነ የወገን ችግር ቅስቀሳ ማካሄድ እንደሚገባ ለልኡካኑ ከአደራ ጭምር አስታውቀዋል ።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በየክፍላተ ሀገሩ ለሄዱ ልኡካን በረሀብ አለንጋ ስለሚሰቃዩ ወገኖቻችን ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጠውና በየክፍላተ ሀገራቱና በየ አብያተ ክርስቲያናቱም የዚሁ የነፍስ አድን ቅስቀሳ ያላሰለሰ ጥረት እንዲያደርጉ ያስረዱ ዘንድ መሪ ትእዛዝ ሰጥተዋቸዋል። በመጨረሻም ተልእኮው የሰመረና መልካም ውጤትም እንደሚገኝበት ከመልካም ምኞት ጋር ገልጸው መሪ ትእዛዝ ሰጥተው፡ አሰናብተዋቸዋል ።

የሥምሪት አራት ከመጋቢት ፭/ ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ቀጥሎ መጋቢት ፲፭/፲፱፻፸፯ ዓ/ምተጠቃልሎአል በየሀገረ ስብከቱ የተላኩት መልእክተኞች ተልእኮአቸውን አከናውነውወደ አዲስአበባ በሰላም ተመልሰዋል ። በኤርትራ ሀገረስብከት በአሥመራ ከተማ የሰንበቱ ልኡካን የሥምሪ አራት ከመጋቢት ፭/፲፱፻፸፯ ቀጥሎ መጋቢት ፲፭/ ፲፱፻፸፯ ዓ/ም አጠቃልለዋል ።

በኤርትራ ሀገረ ስብከት በአሥመራ ከተማ የሰነበቱት ልኡካን በፕሮግራሙ መሠረት እሁድ መጋቢት ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በአሥመራ ከተማ አብያተ ክርስቲያናት የስብከተ ወንጌል ትምህርት ሰጥተዋል እንዲሁም ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ከማከናወናቸውም በላይ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በሊ/ትጉሐን ሙሴ ዓለሙ አስተባባሪነት ለሰሚናሩ ተሳታፊዎች ፤ መጋቢት ፲እና ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም።

ሀ/ ስለ ስምሪት አራት ሰሚናር ዓላማና ተግባር
ለ/ በድርቅ ስለ ተጎዱት ወገኖቻችን እስከአሁን ስለተደረገው ርዳታና ወደፊትም ስላለውዕቅድ
ሐ/ የሰበካ ጉባኤን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ወደፊት ሊደረግ ስለሚገባው ጥረት
መ/ ስለስብከተ ወንጌልና የሰንበት ት/ቤቶችዓላማ
ሠ/ ስለነባር የቤ/ክርስቲያን መንፈሳዊ መምህራንና ተማሪዎች እንክብካቤ
ረ/ ስለጋዜጦችና መጽሔቶች ሥርጭት
ሰ/ በስምሪት ፫ ስለተላኩ ቅጾች አመዘጋገብ
ሸ/ ስለገንዘብ ገቢና ወጭ ማመዛዘን
ቀ/ ስለሂሳብ አያያዝና አሠራር እንዲሁም በየአውጃው ስለሚከፈለው አስተዋጽኦ ፤
በ/ ስለቅርሳቅርስና አጠባበቅ አመዛጋገብ
ተ/ ስለሰበካ ጉባኤ ሥራዎች በየተራ ትምህርታዊ መግለጫና አስፈላጊውን መመሪያ ሰጥተዋል ።

ልኡካኑ ተልእኮአቸውን በዚሁ መልክ ካከናወኑ በኋላ በአሥመራ ከተማ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጥቂቶቹን ጎብኝተዋል ። ፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት በሬእስ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመልአከ ጽዮን ኃይለ አስጉብኝነት የአልባሳቱን የመጽሐፍቱንና በጠቅላላ የንዋየ ቅድሳቱን አያያዝና አጠባበቀ የሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤትንና የመኪና ጽሕፈት/ት/ቤተን ፤ የኢየሩሳሌም ድርጅት ቅርንጫፍ መ/ቤትንና ለዳቦ መጋገሪያ የተሰራውን ሕንፃ ፤ እንዲሁም ከ፶ ሺህ ብር ባላነሰ ወጭ የተሠራው የውኃ ጉድጓድና የመንፈሳዊ ት/ቤተን አንድ በአንድ ተእየተዘዋወሩ ገብኝተዋል ።

የደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን ዓላማ ዋና ይዘትዋ ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም መልካም አርአያና ምሳሌ ከመሆንዋም በላይ በኤርትራ ሀገረ ስብከት በአልሳት በመጻሕፍትና በንዋያተ ቅድሳት በኩል ራሳቸውን ያልቻሉ አብያተ ክርስቲያናትም አስፈላጊውን ሁሉ እየሰጠች እንደምታቋቁማቸው በደብሩ አስተዳዳሪ በመልአከ ጽዮን ኃይለ ለልኡካኑ ተገልጾላቸዋል ።

የሥምሪቱ ቡድን ጉብኝቱን በመቀጠል በ፴፭ኛክፍለ ጦር ክልል ውስጥ የሚገኘው ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክርስቲያንና በመልአኩ ስም ብዙ ሕሙማን የሚፈወሰውን ጸበል ፤ እንዲሁም በቤ/ክርስቲያኑ ዙሪያ የለሙትን አጸዶች በመልአከ ፀሐይ ገብረ ሥላሴ ወልደ ተንሣይ አማካይነት ጎብኝተዋል ። ይህም ቤ/ክርስቲያን ተሠርቶ ፍጻሜ ሊደርስ የቻለው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የተቀደሰ ችሮታ እንደ ሆነም መልአከ ሐፀይ ገብረ ሥላሴ አክለው አስረድተዋል

የክፍለ ጦሩ ንስሐ አባት የሆኑት መልአከ ፀሐይ ገብ





www.ethiopianorthodox.org

ረሥላሴ ለሀገራቸውና ለቤ/ክርስቲያናቸው ያላቸው ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ ለመግለጽ ቃላት ባናገኝለትም ፡፡መልአከ ፀሐይ ገብረ ሥላሴ ከጀግኖች ኢትዮጵያውያን ወገናቻቸው ጎን በመሰለፍ ጠላትን ከማርበትበታቸውም በላይ ሌት በሰዓታትና በቅዳሴ በሌላው መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ እናት ቤ/ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ይገኛሉ ፡፡

የቤ/ክርስቲያኑ ሥራ በራሳቸው ፕላን አውጭነትና በራሳቸው አናፂነት እየተከታተሉ ከፍጻሜ አድርሰውታል ዙሪያውንም በአፀድ ለማሸብረቅ ዛፎችን በመትከል ባሁኑ ወቅት የሚታየው የዛፍ ተከላ ልማት በጣም የሚያስደስት ነው ፡፡

ልኡካኑ ከዚህ ጉብኝት በኋላ በማይተመናይ አዲስ የተሠራውን የኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያንን በባላምበራስ ተክለ አብ አማካይነት ጉብኝተዋል ቤ/ክርስቲያኑ ምንም እንኳ አዲስ ቢሆንና ብዙ ድርጅት ባይኖረውም ይዞታው እጅግ የሚያስደስት ነው ፡፡ የሰንበት ት/ቤትም ተቋቁሞ በጥሩ ሁኔታ እንደሚገኝ ቡድኑ ተመልክቶአል ፡፡ የሰንበት ት/ቤቱ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ሰበካ ጉባኤ እንዳይለየውና አስፈላጊውም ሁሉ እንዲያሟላለት ልኡካኑ በወቅቱ የአደራ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ፡፡

የጉብኝቱ ስነ ሥርዓት በመቀጠል ልኡካኑ ወደ ደብረ ግዕዛን መድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን በማምራት ከሥፍራው ሲደርሱ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሥልጣናት ገብረ ሐዋርያት ሀብተ ሥላሴ ተቀብለዋቸዋል ፡፡ ከዚያም ወደ ቤ/ክርስቲያኑ ውስጥ በመግባት በቤ/ ክርስቲያኑ ውስጥከአዳም ማለት ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራእየ ዮሐንስ ድረስ ያለውን የአበው የነቢያት የጌታችንና የሐዋርያት ሥዕላዊ ታሪክ እየተዘዋወሩ ጉብኝተዋል ፡፡ የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያና አያያዝም በመልአከ ሥልጣናት ገብረ ሚካኤል አማካይነት ተመልክተዋል ፡፡ በዚሁ ደብር ልዩ ልዩ መንፈሳውያን መምህራን ሊቃውንት እንደሚገኙና በዚሁ ደብር የሚማሩ ደቀ መዛሙርትም በስነ ሥርዓት እንደሚጠበቁም ለቡድኑ ተገልጾለታል በአሥመራ ለሥምሪት አራት የተላከው ቡድን ተልእኮውን በዚሁ ዓይነት አከናውኖ መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሶአል ፡፡



ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ለሥምሪት አራት ልኡካን መመሪያ በሰጡበት ወቅት



# ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕትና ቅዱስ የተባሉትን የተግባርና የክብር ስም እንዴት ሊያገኝ ቻለ ? እኒህስ መልካም ስሞች ሊሰጡ የሚችሉትን ምን ዓይነት ተግባር ለፈጸሙ ሰዎች ነው? የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል እንደተባለውም እንዲህ ያሉት የተግባር ስሞች የሚሰጡት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ፤ ስለወንጌል መስፋፋት ፤ ስለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው ላቀረቡ ፤ የሚሰጥ እንጂ በደጅ ጥናት ወይም በባለሟልነት የሚገኝ ምድራዊ ሹመት አይደለም ፡፡

ስለዚህም አምላካችን እግዚአብሔር «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ባለው መሠረት አያሌ ሰማዕታትና ቅዱሳን ይህን ቅዱስና ሰማዕት የተባለውን ቃል በተግባር ለተመርጎም እና የክብር ስም ለማግኘት በሥራቸውና በአካሄዳቸው ክርስቶስን መስለው ፤ እንደሱ ሌላውን በማገልገል ብዙ ተጋድሎ ፈጽመዋል ፡፡ ይህን ብቻ አይደለም ለራሳቸውም ሳይኖሩ ለሌላው እየኖሩ ፤ ስለሌላው ራሳቸውን እየካዱና በሰው ፊትም እየመሰከሩ ቅዱስና ሰማዕት የተባለውን የተግባርና የክብር ስም ሊያገኙ ችለዋል ፡፡ ቅዱስና ሰማዕት የተባለው የክብር ስም በዚህ መንገድ የሚገኝ መሆኑን ከተረዳን ዘንድ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታሪክ ከመዘርዘራችን በፊት ቅዱስ ጊዮርጊስ የፈጸመው ተጋድሎ ጠለቅ ብሎ እንዲገባን አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን የተነሣ አንድ አፍሪካዊ ጀግና ነበር ፤ አገሩ ለብዙ ዘመን በቅኝ ገዥዎች ተይዛ ስለነበር፤አገር ከሌለ ቤተ ክርስቲያንም የለችም ፡፡ ሃይማኖትም የለም ወንጌል መስበክም ማስተማርም አይገኝም መጸለይም አይቻልም ፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከነሰዎቿ የዘመቻው ተካፋይ እንድትሆን ማለት በጾም በጸሎት እንድትረዳ ፡፡ ጀግኖችና ልበ ቆራጥ የሆኑትም ሰዎች እንዲከተሉትና ስለሌላው ተላልፈው እንዲሞቱ በኋላውም እንዲከተሉት ሰብስቦ ነገራቸው ፡፡ ነገሩ የገባቸው እንከተልሃለን ሲሉት ነገሩ ያልገባቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ምን ያህል ደመወዝ ትከፍለን አለህ ሲሉ ጠየቁት ጀግናውም መልሶ መከራን ፤ ስደትን ፤ ዱር ለዱር መንከራተትን ፤ መራብን ፤ መጠማትን ፤ መራቆትንና መሞትን እሰጣችኋለሁ ለጊዜው ደመወዛችሁ ይህ ነው የመጨረሻ ዋጋችሁን ግን ድልንና ነጻነትን ከውድ አገራችሁ ጋር አስረክባችኋለሁ አላቸው ይባላል ፡፡ ቅዱሳንና ሰማዕታትም ቅዱስንና ሰማዕት የተባለውን የክብር ስም አገኝተው ድልን ተጎናጽፈው ወደ ዘለዓለማዊ አገራቸው የሚገቡት በዚህ አንጻር ነው ፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ ምእመናን ቅዱስ የተባለውን ስም በእንዴት ያለመንገድ ሊያገኙት እንደ ቻሉና መከራም ከክርስቶስ ፍቅር ሊለያቸው እንደማይችል ሲጽፍ ከክርስቶስ ፍቅር ግን ማን ይለየናል? መከራ ወይንስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ረሀብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ሲል አስተምሯል (ሮሜ ፰ ቁ ፴፭—፴) በየጊዜው የተነሡት ቅዱሳንና ሰማዕታትም ወንጌልን ከማስተማር ፤ በአደባባይ ቆሞ በሰው ፊት ከመመስከር ፤ ስለ ክርስቶስ ከመናገር ረሀብም ሆነ ስደት ሰይፍም ሆነ እሥራት ሊያግዳቸው አልቻለም ፡፡



ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕተ ልዳ

ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስም ይህንን መሠረት አድርጎ ነው የ፯ ዓመት ተጋድሎውን ሊጀምር የቻለው ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ አባቱ ዘረንቶስ ሲሆን እናቱ ቴዎብስታ ትባላለች እሷም ፍልስጥኤማዊት ናት ቅዱስ ጊዮርጊስ ጥር ፱ ቀን ፪፻፸፯ ዓ/ም ተወለደ የተውለደባትም ሀገር ቀጶዶቅያ ትባላለች ፡፡ ይህችም አገር በቀድሞ አጠራር ትንሿ እስያ ስትባል በዛሬው አጠራር ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ በፋርስ ውስጥ እንደምትገኝ ይነገራል ፡፡ አባቱ ወታደር ነበር በሞተም ጊዜ ከአባቱ ቦታ እንዲተካ ቅዱስ ጊዮርጊስ በወታደርነት እንዲያገለግል ተጠራ ፡፡ አገሩንም በወታደርነት አገልግሏል ፡፡ ፈረሰኛ ወታደርም ነበር ፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ፈረስ በመጋለብ ጦር በመወርወር ስለአደገ በሠራዊቱ መሐከል ታላቅ መወደድን አተረፈ ከጠላት ጋር ጦርነት በሚደረግበት ወቅት ሁል ጊዜ ድልን ስለሚያስገኝና በአመራርም በኩል በአለቆችም በሠራዊቱም ዘንድ ታላቅ ተወዳጅነት ነበረው ፡፡ የሹመትም የማዕረግም ዕድ



www.ethiopianorthodox.org

ገት ሽልማትም ብዙ ጊዜ አግኝቷል ። በመጨረሻ ግን ወንጌል ማስተማርን መረጠ ምክንያቱም አገሪቷ በአምልኮ ባዕድ ተበክላ ስለነበር ሕዝቡን እንዲህ ካለው አምልኮ ባዕድ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ለመመለስ ነው ሥራውንም የጀመረው መልክ ያላቸውን እንስሳት እየመረጡ ለጣዖትና ለአድባር መሥዋዕት ከማቅረብአልፈው የወለዷቸውን ልጆች እንኳን ሳይቀር ለዘንዶ ግብር ያቀርቡ ነበሩ ።

ቅዱስ ጊዮርጊስም እጅና አግሯን ታሥራ ለዘንዶ ግብር እንድትሆን የቀረበችውን ቢሩታዊትን ከእስራቷ ፈትቶ ዘንዶውንም በጦር ገድሎ ስላዳናት ይህንን ያየ ሕዝብ ሁሉ ቅዱስ ጊዮርጊስን ወደደው በሥራውም አመነበት የእሱንም አምላክ እግዚአብሔርን አመለከ። የብዙ የጣዖት መቅደስንም አፈረሰ ሰዎች እየተሰበሰቡ የሚያመልኩባቸውን ዛፎች ቆርጦ አቃጠለ ይሁን እንጂ ሥራው በሕዝብ ዘንድ ቢወደድም ወርቁን ብሩን እያነጠሩ ከወርቅና ከብር ጣዖት የሚሠሩት አንጠረኞችና ከእነሱ እያሰሩ ጣዖት የሚሸጡት ባለጠጎች ታላቅ ተቃውሞ አስነሡበት በሃይማኖት እያሳበቡ ከንድዮቅልጥያኖስና ከግብረ አበሮቹ ጋር ያጣሉት ጀመር ቅዱስ ጊዮርጊስም በየጊዜው እየታሠረ ቢደበደብም ቢገረፍም ብዙ መከራ ቢፈጸምበትም በደስታ ከመቀበል በቀር የማይሰለቸው ሆነ ።

በመጨረሻም ለ፯ ዓመት ከተጋደለ በኋላ ሚያዝያ ፳፫ቀን ፫፻፫ ዓ/ም በአላውያን አደባባይ በሰይፍ ተከልሎ ሞተ ። በልዳም ተቀበረ የመንፈስ አርበኛ የሆነው ቅዱስ ጊዮርጊስ መከራውን ታግሦ የዚህን ዓለም ስቃይ ጨርሶ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ተሻግሮ የሰማዕትነቱን ዋጋ ከፈጣሪው ተቀበለ ።

እርግጥም ቅዱስ ጳውሎስም ሆነ የአፍሪካዊ ጀግና እንደተናገሩት እሱን የመሰሉት የመንፈስ አርበኞች ካል ሡሩ ደሞዛቸውን አይቀበሉም ወደ አገራቸውም አይገቡም ሩጠ የቀደመ እንጂ የሮጠ ሁሉ የድል አክሊልን አያገኝምና ቅዱስ ጊዮርጊስም መልካም ገድል ስለተጋደለ ፤ ሃይማኖቱ ንም ጠብቆ ሩጫውንም ስለጨረሰ የክብር አክሊልን አገኘ

ለምሳሌ የተጣራ ውሃ ለማግኘት ከወንዙ ትልቅነት አይደለም ። ከትንሹም ምንጭም ቢሆን ጥሩ ውሃ መጠጣት ይቻላል ከትልቅ ግንድ ቅርንጫፍም የእሳት ብርሃን አይገኝም ከአንዲት ትንሽ ክብሪት ጫፍ ግፍ ብርሃን ይገኛል የሰማዕትነትም መልካም ሥራ በትልቅነት ክርስቲያን በመሆን ብቻ አይገኝም እንዲህ ያለውም የክብር ስም በሥራ አማካይነት ከትንሽም ከትልቅም ሊወለድ ይቻላል ቅዱስ ጊዮርጊስ የቅዱስነትንም ሆነ የሰማዕትነትን ስም ያገኘው አክሊልንም የተቀዳጀው በሥራና/በእምነት በመጋደል እንጂ ከትልቅ በመወለድ አይደለም ።

አውግስ ጦስ የተባለው ሊቅ ስለዚህ ሲናገር «ታላቅ ሰው ለመሆን ትፈልጋለህን? እንግዲያስ ትንሽ ሰው በመሆን ጀምር በሥራህ ታላቅ ትሆናለህና በርትተህ ከሠራህ ትንሹንም ሥራ ትልቅ ሥራ ታደርገዋለህና ህንጻም ቢሆን መጀመሪያ ትንሽ ሆኖ በሥራ ብዛት ከፍ እያለ ይሄድና ታላቅ ሕንጻ ይሆናል ። አንተም ከሠራህ እንደዚህ ታድጋለህ ብሏል ። ቅዱስ ጊዮርጊስም ታላቅ የክብር ስም ያገኘው ፈተናውን መከራውን ድል አድርጎ ስለተላለፈ ነው ። ቅዱስና ሰማዕት ሊባል የቻለው ። ቅዱስ የተባለውን ስም እንዴት ሊያገኝ ቻለ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰማዕትነት አርፎ ልዳ በምትባለው አገር እንደ ተቀበረ ታሪክ ይነግረናል። ከሞተ በኋላ በየጊዜው የተነሡ ሊቃውንት ጊዮርጊስ የፈጸመውን ቅዱስ ተግባር ለ፫፻ ዓመት ከአጠኑ በኋላ እውነተኛውን ታሪክ አቀረቡ ። በ፭ኛው መቶ ዓመት በደቡብ ሶርያ በምትገኘው ኤድራ ወይም (ይድራስ) በምትባለው ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ና ቅዱሳን አባቶች ተሰብስበው እውነተኛ ሰማዕትነቱንና ቅዱስነቱን በሲዶስ አጽድቀውለታል ። ውሳኔውንም ለሕዝብ አስተላልፈዋል ።

ሰማዕትና ቅዱስ እንደተባለ ከላይ የተጠቀሱትን ታሪኮች ሁሉ በሚገባ እንደፈጸመ በግሪክ በኮፕቲክ ፤ በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተጽፏል ። ይልቁንም በሀገራችን በስንክሳርና በራሱ ገድል ተጽፎ ስለሚገኝ ማንበብ ይቻላል ።


እንግዲህ ቅዱስ ጊዮርጊስ በተጋድሎ ቅዱስ የተባለውን የክብር ስም እንዳገኘ ተረድተናል ። በዚህ አንጻር ለእያንዳንዳችንም የጸጋ ስጦታ ተሰጥቶናል ። አገልግሎት የተሰጠን በችሎታችን ያልተሰማሩትን ለማስተማር አንትጋ ። ምክር አዋቂዎች የሆንም አማካሪ አጥተን ግራ የገባቸውን ሰዎች ከችግራቸው የሚድኑበትን ምክር እንስጣቸው የመስጠት ጸጋ ያገኘን ሰዎችም የሚበሉት አጥተው ለሚራቡት ምግብ የሚለብሱትን አጥተው ለሚራቆቱ ልብስ የልግስና እጃችንን እንዘርጋ ። ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንበል የተጣሉትንም ደግሞ አስታርቀን በመካከላቸው ሰላም እንዲገኝ እናድርግ ሰማዕትነትም ሆነ ቅድስና የሚገኘው አክሊልም የሚሰጠው ይህን ለፈጸመ ስለሆነ ዓለማችንን ለዚህ ተግባር እናውለው ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ታሪክ

የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት የምትገኘው ከአዲስ አበባ ከተማ በስተሰሜን ምሥራቅ ነው ይህችም ገዳም በገደል የተከበበችና በሁለት ወንዞች መካከል የምትገኝ ናት ዙሪያዋም በልዩ ልዩ ዕጸድ ያጌጠችና ሰፋ ያለ ታሪክ ያላት ገዳም ነች ።



የእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

ታቦቷ ሰሚ ነጠበኗ ፈዋሽ የሆነች ብዙ አስደናቂ ተአምር የሠራችና የምትሠራናት የአመሠራረቷም ዝርዝር ታሪክ እንደሚከተለው ይገለጻል ይህች የኪዳነ ምሕረት ታቦት በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በረከት ከሚባለው ቦታ ላይ በ፲፰፻፲፬ ዓ/ም ጥር ፲፭ ቀን በዓለ ጥምቀትን ለማክበር የበረከት ኪዳነ ምሕረትና የአብዩ ገዳም መድኃኔ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን በዋዜማው ዕለት ጥር ፲ ቀን ታቦቶቻቸውን በረከት ላይ አውርደው በድንኳን አስቀምጠው በሠሩት ዳስ ካህናትና ምእመናን ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ሲበሉና ሲጠጡ የማይገባ ሥራ ሲሠሩ የስብሐተ ማኅሌቱ አጀማመርና የቅዳሴው የመግቢያ ሰዓት በማለፉ የበቃ ባሕታዊ ተገልጾ እናንተ ካህናትና ምእመናን ሆይ በዚህ በታላቁ በዓለ ጥምቀት የሚገባችሁን ሥራ ትታችሁ የማይገባችሁን ሥራ በመሥራታችሁና የቅዳሴውን የመግቢያ ሰዓት በማሳለፋችሁ ቅዳሴ ውን በወቅቱ ቅዱሳን ቀድሰውታል በእናተ ግን መትዓ ታዞባችኋል አላቸው እነርሱም ደንግጠው አባታችን ሆይ ለዚህ ጉዳይ ምን ይሻለናል አሉት ።

ኢየሩሳሌም ኼዳችሁ በጌታ መቃብር በጎልጎታ ካላለቀሳችሁ ከመዓቱ አትድኑም አላቸውና ተሠወረ እነርሱም ጉዳዩ አሳስቧቸው በኅብረት ተስማምተውም ታቦቶቻቸውን እንደያዙ ወደታዘዙበት ወደኢየሩሳሌም ለመኼድ ዛሬ የካ ሚካኤል ተብሎ በተሰየመው አድርገው



www.ethiopianorthodox.org


ሲጓዙ እንጦጦ ዓንባ ሥር እስካላ ወንዝ ዙሪያውን በገደል ከተከበበች ቦታ በ፳ ፸፬ ዓም ጥር ፲፰ ቀን ደርሰው በዚች ቅድስት ቦታ ላይ ዕረፍት አድርገው የሾላውን ፍሬ እየተመገቡ ተቀምጠው ሳለ ክርስቶስ በኅልማሳ ሰው ተመስሎ ድንገት መጥቶ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ወዴት ትሔዳላችሁ አላቸው ወደኢየሩሳሌም አሉት መልካም ነው እኔ እመራችኋለሁ ተነሡ ተከተሉኝ አላቸው እነርሱም ተዘጋጅተው ታቦተ መድኃኔ ዓለም ሲነሣላቸው ታቦት ኪዳነ ምሕረት ግን አልነሣላቸው ብላ ችግር ስለተቸገሩ በዚህ ጉዳይ ምህላ ይዘው ሲጸልዩ እመቤታችን የብርሃን ልብስ ለብሳ በገሃድ ተገልጻ እኔ ከዚች ቦታ አልኼድም ይህች የተአምራቴ መገለጫ ናትና ብላ የቆመችበትን ቦታ በእግሯ ሦስት ጊዜ ብትረግጠው ፈዋሴ ዱያን የሆነ የሚያስደንቅ ጠበል ከመሬቱ ፈለቀ ምእመናኑም ይህ ተአምር በዓይናቸው አይተው ካደነቁ በኋላ ለእመቤታችንም በግንባራቸው ተደፍተው ሰገዱ ጠበል ለመሆኑም ምልክቱ አጋንንት ሲጮሁ ሰማይ በቀስተ ደመና ሲሸለም ሕሙማን ሲፈወሱ ታይቷል ጌታም ጉልማሳ መስሎ ሊመራቸው የተነሣው ኪዳነ ምሕረትን ከዚሁ ትታችሁ ታቦተ መድኃኔ ዓለምን ይዛችሁ ወደታዘዛችሁበት ሀገር ጉዞአችሁን ቀጥሉ ብሎ መከራቸው እነርሱም ምክሩን ተቀብለው በዘመናቸው ይህን የመሰለ አስደናቂ ታሪክ በመደረጉ ተመልክተውና ሰምተው ለፈጣሪያቸው ከፍ ያለ ምስጋና አቀረቡ ታሪኩንም ዜና አበው በሚባለው መዝገባቸው ጽፈው ያዙት ታቦተ ኪዳነ ምሕረትንም ውለው ካደሩበት ሾላ ዛፍ ከግንዱ አንድ ክፍል ኪስ ፈልፍለው በማስጊባት ሳንቃ ገጥመውለት ሲያበቁ አንቺ ታቦት ተአምራትሽ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ አያቋርጥ ብለው መርቀው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

እነዚህም አበዎች በዋልድባ ተሠውረው የቀሩ ናቸው ይህችም ታቦት በዚችው አሽከላ ወንዝ በተባለችው ቦታ በሾላ ዛፍ ግንድ ፍልፍል ተሠውራ ብዙ ዘመን ስትኖር የሮሙ ተወላጅ አባ ሊባኖስ የተባሉ ጻድቅ መነኩሴ ወደኢትዮጵያ መጥተው በኤርትራና በትግራይ በመልካ መልዛ ክፍለ ሀገሮች እየተዘዋወሩ ጠበል በማፍለቅና ተአምራት በመሥራት ብዙ ገዳማትንና አድባራትን በመነብኘትና በማቅናት ብዙ ትሩፋት ከሠሩ በኋላ በ፳፪ ዓ/ም ላይ ወደሸዋ መጥተው ዛሬ ሐመረ ኖኅ በፊት አሽከላ ወንዝ ከተባለችው ከዚች ቦታ ለመቀመጥ እቅድ አወጡ ከጥቂት ቀን በኋላ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት ተሠውራ የተቀመጠችበት ቦታ በንብ ተከቦ ብርሃን ሲበራበት ያያሉ ጠጋ ብለው ቢመለከቱ ከሾላዋ ዛፍ ግንድ ላይ በግንቃ የተዘጋ ክፍል ይመለከታሉ ያን ቢከፍቱት ዝ ታቦት ታቦተ ኪዳነ ምሕረት የሚል በጽላቱ ላይ ጽሑፍ ያገኛሉ አባታችን አባ ሊባኖስም ይህን ስለአገኙ በጣም ደስ አላቸው ለእግዚአብሔር ከፍ ያለ ምስጋና አቀረቡ በዚሁም መንፈሳዊ ትሩፋታቸውን እየሠሩ ጥቂት ዘመን እንደተቀመጡ ብዙ መናንያን ዓለም እየመጡ በመቀመጥ በርከት አሉላቸው ከዚህ በኋላ ቤተክርስትያን ሠርተው የእመቤታችን የኪዳነ ምሕረትን ታቦት ቅዳሴ ቤት አከበሩ ጠበሏን ከልለው ዙሪያዋን ተክል ተክለው አጸደቁ ከዚህ በማያያዝ የአንድነት ገዳም አቋቋሙ መናንያኑም በፈቃደ እግዚአብሔር ከየአውራጃው በብዛት እየመጡ ይቀመጡ ጀመር አዲስ በተሠራችው ቤተ መቅደስም ስብሐተ እግዚአብሔር ቅዳሴ ይፈጸምበት ጀመር አባታትን አባ ሊባኖስም እንደዚህ አድርገው ካቋቋሙና ከመሠረቱ በኋላ አባ ዘክርስቶስ የሚባሉ ደግ መነኩሴ ለመናንያኑ ሹመውላቸው እንደዚህ የሚል ትንቢት ተናገሩ ልጆቼ ሆይ በሉ ይህችን ቅድስት ቦታ አደራ ሰጥቻችኋለሁ በኋላ ዘመን ታላቅ ቦታ ትሆንላችኋለች አጋንንት ይወገዱባታል የብዙ ቅዱሳን ዓፅም ያርፍበታል ነገሥታትና ጳጳሳት ይሰግዱባታል ብዙ መናንያን መጠጊያ ያደርጓታል ፤ ቤተ መቅደሷም በወርቅና በብር ተጊጣ ትታነጻለች፤ያንድነቱ ገዳም ተሻሽሎ ይቋቋምባታል ብለው ገዳማውያን ልጆቻቸውን ባርከው በመሰናበት እግዚአብሐር ወደአዘዛቸው ኼዱ ።

አባ ዘክርስቶስም ከጻድቁ ከአባ ሊባኖስ ከተሰጣቸው መመሪያ ገዳሟን ያስተዳድሩ ጀመር በዚህም መካከል በ፱ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓፄ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ጉዲት የምትባል ኃይለኛ ተነሥታ የአኵስም ጽዮንን ቤተ መቅደስ ለማቃጠል መነሣቷ ስለታወቀ ንጉሡ አንበሳ ውድም ታቦተ ጽዮንን በምሥጢር አሲዞ ወደሸዋ ተሰዶ መጥቶ ከዚች አሽከላ ኪዳነ ምሕረት ደርሶ ታቦተ ጽዮንን አሳድሮ ወደዟይ ደሴት ሲሄድ ለገዳሟ ብዙ ንዋየ ቅድሳትና ገንዘብ ሰጥቶ ከጠበሏ ተጠምቆ ቦታዋን መርቆ ኼዷል ይህችንም ገዳም በሰላም ብዙ ዘመን ከኖረች በኃላበ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የግብጽ ተወላጅ ጻድቁ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስከግብጽ ወደኢትዮጵያ መጥተው መጀመሪያ ከንጉሥ ላሊበላ ጋር ይገናኛሉ ከዚያም ሊኖሩበት የመረጡበትን ቦታ የዝቋላ አንባን ለማየት ንጉሥ ላሊበላ ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጋር ወደሸዋ ምድር መጥተው ከዚች አሽከላ ኪዳነ ምሕረት ይደርሳሉ ሁለቱም ታላላቅ ቅዱሳን ከጠበሏ ተቀብተው ቦታዋን ባርከው በእንግድነት ካደሩባት በኋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለነበሩት መነኮሳትና ለንጉሥ ላሊበላ ይህች ገዳም ታላቅ ስመ ጥሩ ገዳም ትሆናለች ከዚህች ወደታች የሚታየው ጫካ መናገሻ ከተማ ይሆናል ብለው ተንብየው ኼደዋል ከዚህ ቀጥለው አባ ዘክርስቶስ አርፈው በዚችው ገዳም ተቀበሩ ።

በምትካቸው አባ ክንፈ መስቀል የሚባሉ መንኩሴ ተሾሙ በዘመናቸውም በ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲነግሡ የክርስቶስ ግማደ መስቀሉ ወደመካከለኛው ኢትዮጵያ መጥቶ በደብረ ብርሃንና በመናገሻ ማርያምና በመሳሰሉት ቦታ ላይ ሲያርፍ በእንጦጦ አንባ ላይም አርፎአል መስቀሉን ያጥኑ የነበሩት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ወደ አሽከላ ኪዳነ ምሕረት ወርደው ከጠበሏ ተጠምቀው ቦታዋን ባርከው ተመልሰዋል ።

የገዳሟ መምህር የነበሩት አባ ክንፈ መስቀልም ዐርፈው በዚችው ገዳም ተቀበሩ በዚሁም መካከል የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የኅት ልጅ የእሌኒ ንግሥትልጅ አባ ኤልያስ የሚባሉ ታላቅ መነኩሴ መንነው መጥተው በዚች ገዳም ተቀምጠው ገዳሟን ታላቅ ስመጥር አድርገዋታል። ክርስቲያን ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የተማርከው አንተ ነህናያለ አንተ አይሆንም ብለው አስገደዷቸው በዚህ ጊዜ መልአከ እግዚአብሔር በክንፉ ወስዶ መናገሻ ማርያም ሠወረባቸው ንጉሡም ነገሩ እንደአልተቻለ አውቀው ወደከተማቸው ተመለሱ ንጉሡ ሲሔዱ አባ ኤልያስ በመልአኩ መሪነት ተመልሰው መጥተው በዚችው ገዳም



ተአምረኛ የእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ጠበል

ዓፄ ዘርዐ ያዕቆብም ለሥራ ጉዳይ ወደዚች ገዳም መጥተው የገዳሟን አቀማመጥ የጠበሏን ፈዋሽነት ተመልክተው በማድነቅ ዳሯ እሳት መኻሏ ገነት ትሁን ብለው ብዙ ማደሪያ ሰጧት ከእኅታቸው ልጅ ከጻድቁ ከአባ ኤልያስ ጋርም ተገናኝተው ብዙ መንፈሳዊ ጨዋታ ከተጫወቱ በኋላ የሃይማኖት አባትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ሁነህ ተሹመህ እንድታስተምር ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ ልውሰድህ ብለው ቢለምኗቸው የእኔ ክፍሌ ብሕትውና ነውና አልኼድም አሏቸው ንጉሡም የቤተ

ብዙ ትሩፋት ከሠሩ በኋላ ጌታ ተገልጾ ገዳሟን ባርኮ ወዳጄ ኤልያስ ሆይ ስምህን ጠርቶ ለጸሎት በቆምክባት በዚች ቦታ የሚጸልየውን ዝክርህን የሚዘክረውን ለጸሎት የቆምክባትን መሬት የሚረግጠውን በሥራት ሰጥቸሃለሁ እንደ ወዳጄ ነቢዩ ኤልያስ ክብርህን አበዛዋለሁ በዚችም ቦታ ጠለ ምሕረቴን አለይባትም ብዙ አስደናቂ ተአምር እንዲሠራባት አደርግልሃለሁ ስምህም በዚች ቦታ እንዲታሰብ አደርግልሃለሁ አሁንም ገዳሟን አስፍተህ ብዙ መናንያንን አሰባስበህ ታላቅ ስመ ጥሩ ገዳም





www.ethiopianorthodox.org

ካደረግካት በኋላ በዚችው ገዳም እንደወዳጁ ሙሴ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ መላእክት ይቀብሩሃል መቃብር ህም ሥውር ሆኖ ይቀራል ብሎአቸው ተሠወረ ጻድቁ ኤልያስም ይህን የመሰለ ታላቅ ቃል ኪዳን ከፈጣሪያቸው ዘንድ ስለ ተሰጣቸው ደስታቸው እጽፍ ድርብ ሆነ ጻድቁ አባ ኤልያስም ይህችን ገዳም ከመናገሻ ማርያም ብዙ መነኮሳት አምጥተው የብዙ መናንያን ቦታ ካደረጓት በኋላ በመቶ ሰላሳ ሁለት ዓመታቸው በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነሐሴ ፲፮ ቀን ተሠውረዋል ። ከርሳቸው ቀጥሎ አባ አርከ ብሩክ የሚባሉ ደግ መነኩሴ ተሾሙ እኒህም መነኩሴ ታቦተ ሚካኤልን ከደብረ ብርሃን ሥላሴ ይዘው መጥተው ከዚች አሽክላ ኪዳነሕምረት አዳብለው ገዳሟን በሚገባ ካስተዳደሩ በኋላ በዚችው ገዳም አርፈ ዋል ከዚህ ቀጥለው ዓፄ ንብለ ድንግል ከዚች ገዳም መጥ ተው ተማኅጽኖ አድርገው ከጠበሏ ተጠምቀው በሚመለ ሱበት ሰዓት ታቦተ ልደታንና ብዙ ንዋየ ቅድሳት ሰጥተ ዋት ሄደዋል ። በግራኝ መሐመድ ወረራም ገዳሟ አል ተደፈረችም በዚህ ሁናቴ ገዳሟ በሰላም ስትኖር ዓፄ ሚናስ እንጦጦ እንባ ከትመው ሳለ በድንገት ታመሙ ከአሽክላ ኪዳነ ምሕረት ጠበል አስመጥተው ቢጠመቁ ፈጥነው ስለዳኑ ሳለ ለገዳሟ ብዙ ስጦታ ሰጡ ይባላል ።

በዘመነ መሣፍንት ላይ ደግሞ በገዳሟ ላይ ከፍተኛ በሽታ ተነሥቶ መነኮሳቱ አልቀው ወደ ጠፍነት ደረጃ መድረሱን ጥቂቶቹ መነኮሳት ተመልክተው ታቦታቱን በሦስት ሣጥን አድርገው ከመቅደሱ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍ ረው ቀብረው አስቀመጡቸው ከብዙዘመን በኋላ ከጉጀም መንደገድ ከዋሻ ሚካኤል አባ ስበነ ድንግል የሚ ባሉ ደግ መነኩሴ መጥተው በገዳሟ ተሾመው የጠፋው ንና የደከመውን ገዳም መልሰው በማጠናከር ታላቅ ገዳም አደረጓት ሲቆፍሩ ከተሰወሩበት ቦታ ታቦተ ልደታን ብቻ አገኙ በዚህም ጉዳይ ታቦተ ኪዳነ ምሕረትንና ሚካኤልን ባለማግኘታቸው ምህላ ይዘው ሳለ ከመቅደሱ ውስጥ አንድ አንበሳ መሬቱን ሲምስ አባ ሰበነ ድንግል በሕልማቸው አዩ በተገለጸላቸው ምክንት መሠረት የካቲት ፲፮ ቀን ከመቅደሱ ላይ ድጋሚ ቢያስቆ ፍሩ ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ከታቦተ ሚካኤል ጋር በሣ ጥን ውስጥ አገኟት በዚህም ደስ ብሎአቸው ከፍ ያለ በዓል አደረጉ በዚህ ሁኔታ በሰላም መንፈሳዊ አገል ግሎት ሲፈጸምባት ቆይቶአል ቤተ መቅደሱም ታድሶላ ታል አባ ሰበነ ድንግልም ብዙ ትሩፋት ከሠሩ በኋላ በዚ ያች ገዳም ዐርፈዋል ።

ከርሳቸው ቀጥለው አባ ሽሐ ብርሃን የሚባሉ ተሹ መው ሳለ በ፲፰ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከዚች ገዳም መጥተው ከጠበሉ ፈዋሽነት ከቦታዋ ታላቅነት የተነሣ ተደንቀዋል ከዚህም እያይዘው ይህች ገዳምታላቅ ባለ ታሪክ ትሆናለች ።

በግርጌዋ የሚገኘው ጫካ ታላቅ ከተማ ይሆናል ብለው ተነብየው ብዙ ስጦታ አድርገውላት ቀራንዮ መድ ኃኔ ዓለም የተባለውን ቤተ ክርስቲያን ሠርተዋል ከዚህ በኋላ በዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ከዚች ገዳም ድረስ መጥተው ቦታውን ከተመለከቱ በኋላ ለመነኮሳት አመች መሆኑን ተረድተው የአንድነት የን ፍሮ ገዳም አድርገው ቤተ ክርስቲያኒቱን አድሰው ብዙ ርስት ጉልት ሰጥተው የጥንቱን ሥርዓት አድሰው ገድ መዋታል ከዚህም በኋላ ይህች ገዳም በየጊዜው ብዙ መም ህራን በቅደም ተከተል እየተነሡ ተሹመው አስተዳድረ ዋል ።

ከዚህ ዘመን ጀምሮ ይህች ገዳም እየገነነችና እየታ ወቀች ሄደች ከዚያም በንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክና በአ ቡነ ማቴዎስ ተጠንቶ ይህች ገዳም ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ተብላ ተሰይማለች ሐመረ ኖኅ ማለት የጻድቁ የኖኅ መርከብ ማለት ነው ኖኅ ከጥፋት ውሀ ፍጥረታትን የሚያድንበት መርከብ ሠርቶ ነበር ይህችም ቤተ ክርስ ቲያን ጠበሏ ከፈለቀበት ላይ የተሠራችና ሁለት ወራጅ ወንዝ ካላት አጠገብ ስለሆነች የኖኅን መርከብ ሥራ ይዛ ስለተገኘች ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ተብላለች እንጦጦ የተባለችው ደግሞ ከእንጦጦ ማርያም አጠገብና አዋሳኝ ስለሆነች ነው ይህች ታላቅ ገዳም በጠበሉ ፈዋሽነት በታ ቦቷ ፈጥኖ ሰሚነት ለየአንዳንድ ሰው የም ታደርገው ውለታ እጅግ ከፍ ያለ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያ ኒቱን በማደስ ንዋየ ቅድሳቶቿን በማሟላት የተደረገላት በጎ አድራጐት ብዙ ነውለመዘክርም በዕቃ ቤቷ ይገ ኛል ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ርክ ስቲያን ይህችን ታላቅ ታቦት ተአምርና ክብር ተመልክ ታና አጥንታ የየካቲት ኪዳነ ምሕረት የነሐሴ ኪዳነ ምሕረት የቃና ዘገሊላ ቅዱስ ሚካኤል በዓል በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች አቅራቢና አዘጋጅ ።

አባ ገብ መስቀል ተስፋዬ ገነተ ማርያም ።

## የመተሐራ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና አቋም ፤

የመተሐራ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲ ያን የሚገኘው በሸዋ ክፍለ ሀገር በየረርና ከረዩ አውራጃ በፈንታሌ ወረዳ ነው በዚሁ ከተማ ቀደም ብሎ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን አለ ። ነገር ግን ወዛደሩ ከሚሠራበት ከፋብሪካው የ፫ ኪሎ ሜትር ርቀት ስላለው ሰው ሲሞት ሬሣ ተሸክሞ መሄድ ከማሰልቸቱም ሌላ በምርቱ ላይ ያደረሰበትን የጊዜ መባከን በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ከዚህም በላይ በየዕለቱ ሰንበቱ ከትምህርተ ወንጌል በመ ራቃቸው በሃይማኖታቸው ላይ የደረሰባቸው መቀዛቀዝ በጣም ስለተሰማቸው በአቅራቢያቸው ቤተ ክርስቲያን እንዲኖራቸው ወሳኝ ስለሆነ ለዚህ ቅዱስ ተግባር ተነሣሱ ቤተ ክርስቲያኑን በስኳር ማምረቻ ድርጅት ወዛደሮችና



በአካባቢው ያለው ሠርቶ አደር ሕዝብ በራሱ መ መዋጮ ለማሠራት ከ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ጀምሮ ትግሉን ሲያካ ሂድ ቆየ ። በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ጋትርያርኩ አካባቢውን ከጎበኙ በኋላ ቦታውን ባርከው መሥራት እንደሚቻል በቃል ሙሉ ጥረት በማድረግ ላይ እንዳለ ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት እንደሌለበት በአባባቢው ባሉ ካህናት ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢደረግበትም በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም የተባረከውን ቦታ ለማስከበር ቅጽሩን አሠርቶ ፪ በ፫ ሜትር ስፋት ያላት




ፈቃድ ሰጥተው ተመለሱ አሠሪ ኮሚቴው በአካባቢው ትያ ትር በማሳየትና ልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ የሚያገኝበትን መቃኛ ሠርቶ ታቦቱን አስገባ ከዚያም ሃይማኖት ወዳድ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ሥራ ፍጻሜ እንዲያገኝ በየ



www.ethiopianorthodox.org

ሳምንቱ ሰንበቴ በመጠጣትና ነዳያን በመመጽወት ወደ እግዚአብሔር እያመለከቱ ደጅ መጥናት ጀመሩ ።

ቅዱስ ዳዊት በዘመኑ ታቦተ ጽዮንን በሕንጻ ቤተ መቅደስ ገብታ እንድትመሰገንለት አስቦ የፈለገውን ያህል ባይፈጸምለትም በልጁ በሰሎሞን ጊዜ ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ ባማረ ሕንጻ ውስጥ ሊያስገባት እንደቻለ ሁሉ ጊዜውና ዘመኑ ሲደርስ ጳጉሜ ፭ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ተጥሎ ሥራው መጣደፍ ጀመረ ።

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ሲያልቅ ሕዝበ ክርስቲያኑ ከሃይማኖት ጋር ተዳብለው ከመጡ የዘልማድ ተጽእኖዎች ለመላቀቅ በወሰደው እርምጃ መሠረት ከየዕድሩ በተውጣጡ ፹ ሰዎች ሃይማኖት አፍቃሪ በሆኑት አባቶች ጥናቶች ለ፰ ተከታታይ እሁዶች በቃለ አዋዲው መሠረት የመማሩ ሂደቶች ሲፈጸም ከዚህ የሚከተሉትን ደንቦች አወጣ ።

ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና እምነት ያለው ሁሉ መንግሥት በመደኅሚያ መልክ በየወሩ ከሚሰጠው ጋራ ማሚያ የሚሆነን ስለ ካህናት ደሞዝ ለቤተ ክርስቲያኑ ማስዳደሪያ የሚውልና ተጠንቶ በምእመናኑ ላይ በሚጠየቀው ዓመታዊ አስተዋጽኦ ለመክፈል የተስማማና ተግባራዊ ያደረገ በየጊዜውም ቤተ ክርስቲያኑ ይበጃል ይጠቅማል በሚል ለሚያወጣቸው መመሪያዎች ሁሉ ፈጻሚ የሚሆን ምእመን መታወቂያ ካርድ ያለው

ሀ/ በራሱም ሆነ ከሱ በሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦች ቢሞቱ የነጻ ጸሎተ ፍትሐት የማግኘት ፤

ለ/ የሚወልዳቸው ልጆችና ልዩ ጥቅም ሳይኖራቸው ራሱ የሚያስተዳድራቸው ሁሉ ሀብተ ክርስትናንና ስመ ወልድናን ያለ ምንም ክፍያ በነጻ የማስነሣት ፤

ሐ/ ከዚህ ዓለምበሞትለተለዩወገኖችከሰልስትእስከ ዓመት በየአስፈላጊነቱ የተወሰነውን የመገበርያ ገንዘብ ብቻ በካርኔ ገቢ በማድረግ ጸሎተ ቅዳሴ እንዲፈጸምለት ፤

መ/ ሙታን ከኛ በመለየታቸው ካደረሰብን ኀዘን ሌላ በሕይወተ ሥጋ ያሉ የቤተሰቦቻቸውን ኤኮኖሚ በሚነካ ብድራት ከሚመለሱ ጋርበመገባበዝ ቤተሰብን ማራቆት ፈጽሞ እንዲወገድና ለነዳያን ብቻ እንደአቅሙ መመጽወቱ የሚጠናከርበትን መንፈሳዊ ትምህርትእን ዲሰጥና ለዚህም በምሳሌነትና በመንገድ ጠራጊነት ወደ ቤተ ክርስቲያን በሙታን ተመካኝቶ የሚመጣው እህል ውሃ እንዲቀር ሲወሰን በሌላ በኩል በጥናትና ማኅበራዊ ኑሮን በሚገነባ የፍቅር እንጀራ ተብሎ የሚጠራውን ጸበል ጸዲቅ አይመለከትም ። ይህም ሊሆን የቻለው ባለው የኑሮ ውድነትና ሠራተኛው ከሥራው ሳይዘናጋ በሃይማኖቱ የሚኖረው ፍቅር እንዲጠ ናከር ነው ።

ሠ/ ካህናት የሥራ መደባቸው ታላቅና ቅዱስ ሆነው መንፈሳዊ አገልግሎት ሰጭ ቢሆኑም ቅሉ በሥራ ጠባያቸው በሚከፈላቸው ደሞዝ እንደማንኛውም ሠራተኛ በሚያገኙት በወር የተተመነ ጥቅም ተለዋውጠው መኖር ማለት ይሰጣሉ በሚሰጡት መጠን መልስ የሚፈልጉትን የማግኘት ፍላጎት ክቡር ዓላማቸው የሆኑ ካህናት እንዲቀጠሩ ።

ረ/ የሚቀጠሩት ካህናት ሁሉ ራሳቸውን በራሳቸው በመርዳት የሥራ ክቡርነትን በተግባር በመተርጎም ምሳሌነታቸው ለሰነፎች መቅሰፍት ለሠራተኞች ሕይወት የሚሆኑ አባቶች መሆን አለባቸው ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ የማይሠራ አይብላብሎአስተምሮአል።

ሰ/ የሩቅ አላማችን ዘመናዊ ገዳም ለማድረግ እንደመሆኑ መጠን ሥርዓተ ገዳምን ቀስ በቀስ ሊገባቸው የሚችሉ ካህናት በደብሩ እንዲያገለግሉ ሲደረግ ዕቅዱም በሥራ ውሎአል ።

ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች እንደተጠናቀቁ የሕንጸ ቤተ ክርስቲያን ሥራና የካህናት መኖሪያ ቤት ወደ ፍጻሜ በመድረሱ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ታቦተ ሕጉ ተባርኮ እንደገባ የምእመናኑ ሃሳብ ተከናውኖለት ለእግዚአብሔር ምስጋና ካደረሰ በኋላ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ተግባራዊ የሚያደርግለት የሰበካ ጉባዔ አቋቁሞ በመንፈሳዊ አባትነቱ አብነት ያለውን የደብር አለቃ ሲያስፈልግ ፲፱፻፷፰ ዓ/ም መልአክ አሚን ዘካርያስ ኃይለማርያም የመጀመሪያው የደብር አለቃ በመሆን ለሦስት ዓመታት በሰላምና በቅድስና መንፈሳዊ አገልግሎትን ከመቀጠሉ ሌላ ዓላማችን ዓላማው መሆኑን ከባሕሪው ጋር በመዋሐድ ጥቅምና ጉዳቱን ለየ ። የሰበካ ጉባኤው ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ የገጠሙት መሰናክሎችና ተራ ምቀኝነቶች ያሰለቹት ቢሆንም በተቻለ መጠን በየጊዜው የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የሚበዙበትን መንገድና የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሚቃረቡበትን ዓላማ ከመቀስቀስ በዝና አያውቅም ። ከሞላ ጎደል ሥራ ላይ ካዋላቸው ተግባሮች ፤

፩ኛ/ ከ፩፱፻፸፱ ዓ/ም ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ የሙንታ መዝገብ ቅጽ አዘጋጅቶ በየዓመቱ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ወገኖች በዝርዝር እየጠራ በጸሎተ ፍትሐት ማስታወስ ።

፪ኛ/ ካህናት በዓመት ውስጥ የሠሩትን ማለት ምን ያህል የምእመናንን ቤት ዙረው እንደጎበኙናበዓመትውስጥ በተካሄዱት ጸሎተ ቅዳሴ ላይ እያንዳንዱ ካህን የቀደሰበትን የቀን ብዛትና የአገልግሎት ተሳትፎ ልዩ በዓል በማዘጋጀት ለምእመናኑ በመግለጽ ያላቸውን የተቀደሰ ሥራ ገልጾአል ። ተገልጋዩም ሕዝብ የካህናትን ክቡር ሥራ በማድነቅ የሞራል ድጋፍ ከመስጠቱም በላይ ከዚህም የበለጠ እንዲሰሩ ስለገፋፋቸው ሕሊናቸው በመንፈሳዊ ተመስጦ ተቀስቅሶአል ።



፫ኛ/ ሰበካ ጉባኤው በየዓመቱ የመጋቢት መድኃኔ ዓለም በዓልን በማዘጋጀት ለጸበል ጸዲቅ የሚያዋጣው የበጀት ውጥረት ስለፈጠረበት የእናቶች የዓመት የጽዋ ማኅበር በሚል ሰበካ አቀፍ የጽዋ ማኅበር ከግንቦት ወር ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ጀምሮ በማቋቋም እነሆ በየዓመቱ የጽዋ ማኅበሩ የበዓሉን ዝግጅት በአፀደ ቤተ ክርስቲያን በማዘጋጀት ማንኛውም የቤት እመቤት የበሰለ እህል ውሀ ሳትሸከም የሰበካው እናቶች ሳይበልጡና ሳይበላለጡ ወይም ሳይተናነሱ የእኩልነት በዓላቸውን በደመቀ ሁኔታ እያከበሩ ናቸው ። ✝

ማሳሰቢያ ፤ የሴቶች የጽዋ ማኅበር የተቋቋመበት ዋና ዓላማ

ሀ/ በየዓመቱ የመጋቢት መድኃኔ ዓለም በዓልን በጋራ ለማክበር ፤


ለ/ በቤተ ክርስቲያን የሚጓደሉትን ነገሮች ለማሟላት

ሐ/ የሃይማኖት ትምህርትን ለማግኘት ፤

መ/ የሙት ልጆችን ለመርዳት ጥረት ለማድረግ ፤

ሠ/ እናቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ተሳትፎና ኃላፊነት ለማሳወቅ ፤

ረ/ እናቶች ቅዱስ ወንጌልን ለማዳመጥ የሚኖራቸውን መንፈሳዊ ኃይል ለማጠናከር ናቸው ።



በተራ ቁጥር ፫ ከሀ—ረ በተዘረዘሩት ዓላማዎች የተቋቋመ የጽዋ ማኅበር ከፈጸማቸው ተግባሮች ፤

ሀ/ በ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በዓሉን በሚገባ አክብሮ ከ፩ሺህ ፺፱ ብር በላይ የሚያወጣ አበባ ምንጣፍ ፤ አግዳሚ ወንበር ገዝቶ አበርክቶአል ።

ለ/ በ፲፱፻፹፮ ዓ/ም በዓሉን በሚገባ ካከበረ በኋላ የተረፈውን ለሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት ማሠሪያ ርዳታ ፩ሺህ ብር ጥሬ ገንዘብ ሰጥቷል ።

ሳይወሳ ሊታለፍ የማይገባው ነገር ቢኖር ዜማ ሳይጮሁ ፤ ተሰጥዎ ሳይቀበሉ ፤ የሙጋድ እንጨት ሰብረው ቤተልሔም ሳይጠጉ ከቅኔ ማኅሌት አልፈው ፤ መቅደስ ሳይገቡ ፤ ቡራኬ ከመቀበል በስተቀር ባርከው ሳይሰጡ በቅናት ልባቸው የነደደ አንዳንድ የደብር አለቆች ለበላይ ነገሩን አጣሞ በማቅረብ የሴቶች መሰባሰብ እኛን ካህናትን አባረው ሴቶች ሊያወድሱበት ነው ተብሎ የቀረበውን ክስና ለማሳደድ የተደረገውን ሙከራ ያስታውሳል ።

፬ኛ/ የቅዱሳት አንስት የመድኃኔዓለም ዓመታዊ የጽዋ ማኅበር መቋቋም ከፈጸማቸው ዓበይት ጉዳዮች አንዱ አካባቢው የኢንዱስትሪ ቀበሌ እንደመሆኑ መጠን ሃይማኖት የሚያፈቅሩ ምእመናን በሥራው ጠባይ ቤተ ክርስቲያን ለሰላምና ከበአሉ በረከት ለመቀበል ያለውን የበአሎቻችን አከባበር ችግር በማጥናት የመጋቢት መድኃኔዓለም በዓለ ንግሥ እሁድን በማይለቅና የበዓሉንም የተደራረበ ድምቀትና ተዘናግቶ የቆየውን የበዓለ ጲራቅሊጦስን ቀን በተጨማሪ ለማክበር ሲባል ፤ ወዛደሩም በዚህ ቀን የሚበዛው በዕረፍት ላይ ስለሚውል ፤ ለተሳትፎ እንዲያመች ከ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ጀምሮ የመጋቢት መድኃኔዓለም በዓለ ንግሥ የጲራቅሊጦስ ለት እንዲውል ሕዝቡን በማስተማር የወሰኑት ውሳኔና ያገኙት ተቀባይነት ምንጊዜም በሕያው የሕይወት መዝገብ የሚያኖራቸው ሆኖ ተገኝቷል ።

፭ኛ/ ቤተ ክርስቲያኗ ገቢዋ ያልዳበረና ልጆችዋ አነስተኛ መሆናቸው ሥራውን ማካሄድና ማንቀሳቀስ የሚቻለው ከሕዝቡ የአሠራር ስልት ካላቸው ምእመናን በመሆኑ



www.ethiopianorthodox.org

እድርተኞችንና የእድር ዳኞችን በማሰባሰብ በየዓመቱ ከሞላ ጎደል በበዓለ ጥምቀት ጊዜ ለድግሥ የሚውለውን ገንዘብ በተቻለ መጠን ሥራው ለሚመለከታቸው ካህናትና ከሩቅ ለመጡ ምእመናን ምግብ በማዘጋጀት የተረፈው ለቤተ ክርስቲያን የውስጥ ማደራጃ ይዋል ተብሎ የቀረበው ሃሳብ ተሰሚነት በማግኘቱ ደስ ያሰኛል ።

በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ለበዓለ ጥምቀት ማዘጋጃ ድግስ ተደግሶ ከተፈረው ከ፲፱፻ሸህ፯፻ በላይ ለቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ አልባሳት ተሰፍቶ ተሰጥቶአል ።
በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም እንዲሁ ለጥምቀት በዓል ተደግሶ የተረፈውን ለሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት ማሠሪያ የሚውል ከ፰ሺህ፯፻ ብር በላይ ገቢ አድርገዋል ።
በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በለዓ ጥምቀት ዕለት ደግሞ ባለው የኑሮ ውድነት ምክንያት መዋጮ በርካታ ባይሆንም ከድግስ የተረፈውን ለሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ማሠሪያ የሚውል ከ፫፻ ብር በላይ ገቢ አድርገዋል ።

፯ኛ የሰበካው ምእመናን በቅን ለሚያስተምራቸውና በጥሩ የመንፈሳዊ ስነምግባር ለሚመለከታቸው አባት መከበርናመወደድይህ ነው ተብሎ ግምት ሊጣልበት አይችልም ። ለዚህም ትልቅ ምሳሌ አድኅል ለማቅረብ ለብዙ ዓመታት በቅዳሴአገልግሎት የቆዩት አባ ገ/ማርያም ገ/መስቀል የደብሩ አለቃ ሆነው ሲሾሙት ያደረገው ከፍተኛ አቀባበልና የእራት ግብዣ በየካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ከ፱ በላይ የሚሆኑ አባቶች እናቶችችና ወጣቶች ገንዘብ በማዋጣት በተከናወነው የአለቃው አቀባበል የእራት ግብዣ ላይ ያሳየው ፍቅርና ታማኝነት ለመንፈሳውያን አባቶች ያለውን ክፍተኛ ስሜት በተግባር ተገልጾአል ።

፰ኛ/ በደብሩ የመድኃኔዓለምን በዓል በእናቶች የጽዋ ማኅበር ተጠናክረው በዓላቸውን በማክበራቸው፣ ወንዶች በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣስተው ነሐሴ ፭ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የቅዱስ ገብርኤል የወንዶች አመታዊ የጽዋ ማኅበር ለማቋቋም የሰበካ ጉባኤው ባደረገላቸው ጥሪ በእለቱለት ከደስታቸው የተነሣ ከየኪሣቸው በማዋጣት ከ፰፻ ብር በላይ በረከት በመጣል ዓመታዊ የጽዋ ማኅበር በማቋቋሙ የ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ታህሣሥ ገብርኤል በወንዶች መዋጮ በሚገባ ተከብሯል ። ለወደፊቱም በቋሚነት የሚቀጥል መሆኑን ተረጋግጣአል ።

ቤተ ክርስቲያኑ በየጊዜው ለሚያደርጋቸው የመሻሻልና የዕድገት ደረጃዎች አንዳንድ እንቅፋት ቢኖርም በተቻለ መጠን የተሻሻለና በእግዚአብሔር በኩል ዋጋበሚያሰጥ የሥራ እቅድ እንድንደክምና ለብዙኃኑ ምእመናን አብነት የሚሆን ሥራን መስራት እንድንችል ይህችን መገለጫ የምታነቡ ሁሉ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ያለ ወገን በሙሉ በጸሎቱ እንዲያስበን እየተማጸንን የዚህ ዓመት የመጋቢት መድኃኔዓለም በዓለ ንግሥ ለመጀመሪያ ጊዜ ግንቦት ፳፭ ቀን ፷፮ ዓ/ም በዕለተ ሰንበት የጰራቅሊጦስ ዕለት የምናከብር መሆኑን አውቃችሁ የመድኃኔዓለም ወዳጆችና ፍቅር ያላችሁ ሁሉ በበዓሉ ተሳታፊ እንድትሆኑ ልን በማክበር ጠርተናችኋል ።

የእግዚአብሔር አብ ጸጋ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን፡ አሜን ።

የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት መተሐራ


## ማዕዶት ስለ ዶቤ /ሩቴ/ማሽን ከአባ ተስፋ ሞገስ ጋር ያደረገው የጥያቄና መልስ ንግግር ።

ማዕዶት ይህ የሽመና መሣሪያ ከየት እንዴት ተገኘ
መልስ ይህ /ሩቲ / የተባለው የልብስ ማምረቻ መሣሪያ የተገኘው የአውስትሪያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ካርዲናል ኮኒንግ በጥር ወር ፲፱፻፷፭ ዓ/ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንንበይፋ በጎበኙበት ወቅት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ከፍተኛ የሆነመንፈሳዊ ውይይት ካደረጉ በኋላ አንድ የልብስ ተክህሞ ጨርቅ ማምረቻ ማሽን በነፃ ለመስጠት ቃል በገቡበት መሠረት ነው ። ይህም በአቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የአልባሳት ጨርቅ የሚሠራው ማሽን የሚገኝበትን በፕሮጀክት ከተጠና በኋላ ጥናቱን ይዞ አንድ መልእክተኛ ወደ አስትሪያ እንዲላክ ፤ በመወሰኑ ምክንያት በአቃቂ ጨርቅ ፋብሪካ የምናሠራው ስቲ ጨርቅ/ቸርችዲዛይን/ የሚሠራው መሣሪያ ፋብሪካው የሚገኘው የት አገር እንደሆነየመሣሪያውን መለዋወጫ ዕቃዎች እንዴት ማግኘት እንደሚችል ። የሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ ከሀገር ውስጥ ማግኘት የሚቻል መሆኑ በዝርዝር በፕሮጀት ተጠንቶ እንዲላክልን መ/ቤቱ ለአ ቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ማሳሰቢያ ደብዳቤ ጽፎ ፋብሪካው ስለተባበረን በጥያቄው መሠረት ጥናቱን አጠናቆ ስለላከልን ይህንኑ ፕሮጀክት ይዤ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያሪክና በዋናው ሥራ አስኪያጅ በሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው መልእክት ፈቃድ መልእክቱን ይዤ ወደ አውስትሪያሊያ ቢየና ሄድኩኝ መልእክቱንለሚመለከታቸው ባለ ሥልጣኖች አቅርቤ በጉዳዩ ብዙ ውይይት ከተደረገና ሰፋ ያለ ጥናት ከተካሄደ በኋላ መሣሪያው በቅርብ ጊዜ እንደሚላክ የሰጡትን መልስ ይዤ እንደተመለስኩ በሚያዚያ ወር ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ሪፖርቱን ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክናለዋናው ሥራ አስኪያጅ ለሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው አቀረብኩኝ ።
ከዚህ በኋላ ብፁዕ ካርዲናል ኮኔንግ በገቡት ቃል መሠረት መሣርያው አሰብ ወደብ እስኪደርስ ድረስ ማናቸውንም ወጭ ችለው በመርከብ ልከውልን በመስከረም ወር ፲፱፻፷፮ ዓ/ም መሣሪያው ግምሩክ መድረሱ እንደተረጋገጠ በማርታይም አማካይነት ተገቢውን ወጭ ከፍለን መሣሪያውን ተረከብን ።

ይህ መሣሪያ ክብደቱ ፫ሺህ፰፻ኪሎ ግራም ስለሆነ መሣሪያውን ለማውረድና አሁን ካለበት ቤት ለማስገባት ብዙ ችግር ደርሶብን ነበር፤ሆኖም ልምምድ ባላቸው በአቃቂ ጨርቃጨርቅ ቴክኒሽያኖች አማካይነት በፎርትሊፍት ወርዶ እየተገፋ ብረቱ እየተንከባለለ ወደሥፍራው ሊገባ ችሏል። ላይ ይገኛል ።

አሁን ወደ ጥያቄው ልመለስና የሽመናው መሣሪያ ከየት እንዴት ተገኘ? ለሚለው ጥያቄ ቀደም ብየ እንደገለጽኩት አሁን ካለበት ቦታ አስገብቶ ለመትከልና ለመገጣጠምም ብዙ የባለሙያዎች ጉልበት ፈሰበትና ብዙ ገንዘብ ወጭ ሆኖ ነው፤ለዚሁም በሞያቸውና በእውቀታቸው ሳይሠለቹ የረዱን የአቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ቴክኒሽያኖች ፤ ከላይ ስማ

የግል ቤተ መጻሕፍት



የአልባሳት መሥሪያ ማሽን (ዱቲ)

ከዚህ በኋላ ይኸው መሣርያ ዘላቂ ቦታውን ይዞ እንዲሠራ ለማድረግ የአቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ቴክኒሽያኖች አቶ ክብረ አብ አብርሃም ዋና ቴክኒሺያን አቶ ከበደ ኪዳኔ ረዳት ቴክኒያሽያን አቶ ክፍሉ ሥዩም የመብራት ቴክኒሽያን ሆነው ቅዳሜና እሁድ ዕረፍት ጊዜ አቸውን በመሠዋት በበጎ ፈቃድ መኪና እያቀረብን በማመላለስ በብዙ ድካምና ጥረት መሣሪያውን አሁን ካለበትበመትከልና በመገጣጠም ሥራውን እንዲጀምር ተደርጎ በመሥራት ቸው በዝርዝር የተጠቀሱት በጎ አድራጊዎች ሲሆኑ እንዚህም ለሀገር ለወገንና ለቤተ ክርስቲያን ባላቸው ፍቅር ያለመሰልቸት በመሥራታቸው ነው፤የመሥሪያቤቱ ሹፌሮችም ቴክኒሽያኖችን በማመላለስ ስለረዱን ሳናመስግናቸው አና ልፋም እነሆ አሁን በዚህ ዓይነት ጥረትና ድካም ማሽኑ ተገጣጥሞ ሥራውን ሊጀምር ችሏል ።

ማዕዶት ፤ ለዚህ ሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ከየት ተገኘ?
መልስ ፤ በመጀመሪያ ለዚህ ጉዳይ ሁለቱ የቤተ ክር




www.ethiopianorthodox.org

ስቲያን መሪዎች ተገናኝተው ወይይት ካደረጉና ፕሮጀክቱን ይዞ አንድ መልእክተኛ ወደዚያ እንዲሄድ ከወሰኑበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ለመልእክተኛው የአየር ደርሶ መልስ ፤ ከሆቴል ወጭ ጀምሮ ማሽኑ ተተክሎ ሥራ እስከ ጀመረበት ድረስ ያለውን ለማሽኑ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በመግዛት ከዚያም ወዲህ አሁን ማሽኑ የሚሠራውን ጥሬ ዕቃ ማቅረቢያ የሚያስፈልገውን ማለት የሚጠይቀውን ወጭ ሁሉ ቀደም ብሎ ተቋቋሞ ሥራውን በማከናወን ላይ ካለው ከአልባሳቱ ገቢ ላይ ነው

ማዕዶት ፤ ማሽኑ ሥራውን ከጀመረ ስንት ጊዜ ይሆነዋል ?

መልስ ማሽኑ ሥራ የጀመረው በኅዳር ወር ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ነው ሥራ በመጀመረበት ዕለትም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በሥፍራው ተገኝተው ከመኅብኝታቸውም በላይ ማሽኑም በቴክኒሺያኖቹ አማካይነት ሥራውን ሲያከናውን ተመልክተዋል

መልስ ፤ አንድ ሥራ ሲሠራ ችግር እንደሚያጋጥም የታመነ ነው ፡፡ ሆኖም ችግሩን ተቋቋሞ ያሰቡትን መወጣት አስፈላጊ ነው ፤ ይህ ማሽን በሥራው ማለትበሙያው የሰለጠኑ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ማንም ሰው ሊሠራው አይችልም እነዚህም ቴክኒሽያኖች በነፃ የሚረዱት በትርፍ ጊዜያቸው እንጂ በሥራ ሰዓት ዕረፍት የሌላቸው ስለሆነና በአጭር ጊዜም ሥራ ብዙ መሥራት ስለማይቻል ፤ በ፲ ሰዓት ከሥራ ሲወጡ ወደምሳ እንሂድ ሳይሉ አምጥተን ሲሠሩ አምሽተው ቤታቸው ከፋብሪካው አካባቢ ስለሆነና መልሰን ማድረግ ስላለብን፤ እሁድም እንደ ዚሁ ማምጣትና መመለስ ስላለብን ከብረት ጋር ሲታገሉ ውለው እህል ውሀ ማለት ስላለ በዚህ በኩል ለጊዜው በሰው ኃይልም ሆነ በገንዘብ እጥረት አንዳንድ ጊዜ ችግር ነበር ፤ ሆኖም ስለገንዘቡ ከአልባሳቱ ገቢወጭው እየታዘዘ ሹፌሮችም ትርፍ ጊዜአቸውን መሥዋዕት እያደረጉ ስለተባበሩን ችግሩን ተወጥተን የታሰበው ሥራ ግቡን



አቶ ክብረ አብ አብርሃ ዋና ቴክኒክ



አቶ ከበደ ኪዳኔ ረዳት ቴክኒክ



አቶ ክፍሉ ሥዩም የኤሌ/ ቴክኒሽያን

ማዕዶት ፤ ማሽኑ ባሁኑ ጊዜ የሚያንቀሳቅሰው ሰው ማን እንደሆነ ቢገልጹልኝ ?

መልስ ፤ ነገሩ ቀደም ብሎ ቤቱ ስለአሰበበት ከሐምሌ ወር ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ጀምሮ በሥራው ለመሰልጠን በጎ ፈቃደኞች ሆነው የተገኙት ሠራተኞች ዲ/ ገብረ እግዚአብሔር አገዘና ዲያቆን አክሊሉ መኩንን ወደ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ተልከው ፋብሪካው ባደረገልን ትብብር ለ፩ ወራት ሠልጥነው ተመልሰው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ፋብሪካውም ሰዎችን በማሰልጠንና ነፃ አገልግሎት በመስጠት ያደረገልን ትብብር በቀላሉ የሚገመት ስላልሆነ በዚህ አጋጣሚ ሳላመሰግን አላልፍም ፤

ይህ መሣሪያ እንዴት ተገኘ ለሚለው ጥያቄ እንዴት እንደተገኘ በመጀመሪያ መልስ ሰፋ አድርጌ ያስቀመጥኩት ስለሆነ መድገም አስፈላጊ አይመስለኝም ።

ማዕዶት በዚህ ሥራ ላይ ያጋጠማችሁ ችግር ቢኖር ባጭሩ ቢያብራሩልን?

ሊመታ ችሏል ።

ይሁን እንጂ ሥራው የተከናወነው በትርፍ ጊዜ እንደ መሆኑ መጠን ብዙ መሥዋዕትነት ተከፍሏል የክፍላችን ሠራተኞች ቄስ ሐዲስና ሌሎችም በሥራው ከፍ ያለ ትብብር አሳይተዋል ።

በተለይም አቶ ታደለ ገብረ መስቀል ቴክኒሽያኖቹ ለሥራው የሚመጡት በትርፍ ጊዜያቸው ስለሆነ ከኔም ነሆ ከቴክኒሽያኖቹ ላንዲት ደቂቃ እንኳን ሳይለዩ ትርፍ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ ሥራው ፍጻሜ አግኝቶሲሠራ ለማየት ባላቸው ጉጉት ያሳዩት ትጋት ከፍ ያለ ስለሆነ ሳናመሰግናቸው አናልፍም ።

ከዚህም ሌላ የምሰጠው ማጠቃለያ ሃሣብ ቢኖር ከላይ የጠቀስኳቸው ቴክኒሽያኖች ለሀገር ፤ ለወገን ፣ ለቤተ ክርስቲያናቸው ባላቸው ፍቅር ድካም ሳያሸንፋቸውጨለማ ሳያግዳቸው ከብረት ጋር በመታገል ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለው ይህን ማሽን በሥራ ላይ እንዲውል በማድረጋቸው



አሁንም አንዳንድ ችግር ሲገጥመን በስልክ ስንነግራቸው በራሳቸው ትራንስፖርት እየመጡ ማሽኑን መርምረውና አስተካክለው ለሠራተኞቹም ችግሩን ገልጸውና አስረድተው ይህ ዓይነት ችግር ሲገጥማችሁ ይህን አድርጉ በማለት ምክር እየለገሱዋቸው ስለሚኼዱ እነዚህ ሰዎች አብረው የሠሩትና አሁንም የሚሠሩልን ውለታ እጅግ ብዙ ስለሆነም ደጋግሜ የማቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ ነው ። ዋጋ በገንዘብ ቢተመን በቀላሉ የሚገመት ስላልሆነ ለቤተ

ማዕዶት ፤ ከዚህ በስተቀርስ ለወደፊቱ ያቀዳችሁት ሥራ እንዳለ ቢገልጹልን ?

መልስ ፤ ማሽኑ አሁን የሚሠራው ጥሬ ዕቃ ድሩ በቢም ፤ ማጉ በቀሰም እዚያው እፋብሪካው በማሽን ተሠርቶ እየተዘጋጀ እየመጣ ነው የምንሠራው ፤ የሠራነው

በላይ የሠራነውም ጨርቅ ሥራው የሚያልቀው እዚያው ኼዶ መሆኑን መታወቅ አለበት እላለሁ ።

ማዕዶት፤ ከዚሁ ሥራ ጋር በማከል የምታካኺዱት የልማት ሥራ እንዳለ ቢያብራሩልን ?

መልስ ፤ ከዚህ ሌላ የምናካኺደው ሥራ ቢኖር የአልባሳቱን የሥፌት ሥራ ነው ። ይህ የአልባሳት ማደራጃ ክፍል አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም መጀመሪያ ሲሆን ያሳየው ውጤትም ከፍ ያለ ነው ፤ ይህም ዋና ዋናው ሲጠቀስ አልባሳቱን ጥሩ አገላግሎት እንዲሰጥ እያደረግን በማዘጋጀት በተመጣጠነ ዋጋ መሸጥ በጣም ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት በቅዱስነታቸው ትእዛዝ በነጻ መስጠት ፣ ጳጳሳት ሲሾሙ ልብሰ ተክህኖውን



ዲያቆን አክሊሉ መኩንን



ዲ/ ገብረ እግዚአብሔር አገዘ



ወ/ሮ ምሥክር ሰሎሞን

ነጭ ጨርቅ እንደገና ቸርች ዲዛይን የቤተ ክርስቲያን ዓይነት ታትሞ ከመጣ በኋላ ነው አልባሳት የሚሠራው ፣ ይህን ሁሉ እዚህ አሟልቶ ለመሥራት ይህን ሁሉ የሚያጠቃልሉ መሣሪያዎች ማምጣት ይኖርብናል ። ወይም ራሱ ዲዛይን አውጥቶ እንዲሠራ ከተፈለገ የሀር ድርና ማግ የተለያየ መልክ ክር ማለት ጥሬ ዕቃ ማግኘት አለብን ይህን ሁሉ አሟልቶ ለመሥራትም ብዙጥረት ያስፈልጋል ቢሆንም ከፊሉን ጠይቀናል እንደምናገኝም ተስፋ አለ ሌላውን ለማግኘት መጀመሪያ ባገኘነው መሣሪያ ሠርቶ ጥሩ ውጤት ማሳየት አለ ርዳታ ሰጭዎቹ ውጤቱ አጥጋቢ መሆኑን እየተከታተሉ ስለሆነ ይህን ለማድረግ አሁንም በጣም ጥረት አስፈላጊ መሆኑን ደጋግሜ እገልጻለሁ ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ጥሬውን ዕቃ የምናገኘው ከአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ እየገዛን ከመሆኑም

በማዘጋጀት ፣ ቅዱስነታቸው ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት በነጻ እንዲሰጥ የሚቀርበውን ጨርቅ በነጻ በመስፋት ይህንና ይህን የመሰለ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ከመሆኑም በላይ ለሚዘጋጀው አልባሳት መጠነኛ እያስከፈለ በብዙ ሺህ ለሚቈጠሩ አብያተ ክርስቲያናት አድርሷል ።

ስለዚህ ይህን ሥራ በሰፊው ለማስፋፋትና አልባሳት ብቻ ሣይሆን ሠራተኞቹን በልብስ ስፌትና በዕቅድ ሥራ በይበልጥ አሰልጥኖ የጳጳሳትን የመነኮሳትንና የካህናትን ልብስ በሚገባ ለማዘጋጀት ዕቅድ አለ ይህን ሁሉ ለማድረግ ሠራተኞቹ እንክብካቤ ለሥራውም ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ብድርቅ ለተጎዱት ወገኖች የድንኳን ርዳታ አደረጉ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባለባቸው መንፈሳዊ ናብሔራዊ ኃላፊነት ባለፈው ጊዜ በትግራይ ክፍለ ሀገር የመጠለያ ጣቢያ ተገኝተው በርካታ ችግረኞች በመጠለያ እጥረት ምክንያት ለሀሩርና ለብርድ የተጋለጡ መሆናቸውን ከተመለከቱ በኋላ ይህን አሰቃቂ የወገን ችግር ከመንግሥት ጎን ተሰልፎ ለመቋቋም በወሰዱት ርምጃ በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎችንና የሰበካ ጉባኤያት፣ምክትል ሊቃነ መናብርትን እንዲሁም በቤተ ክህነት ሥር የሚተዳደሩ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎችን ሰብስበው የችግሩን ጽናት በዝርዝር በማስረዳት የመጠለያውን እጥረት ለማስወገድ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶቹ አቅማቸው በፈቀደ መጠን እያንዳንዳቸው አንዳንድ ድንኳን አሰፍተው እንዲያበረክቱ በሰጡት አባታዊ መግለጫና መመሪያ መሠረት አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶቹ የተሰጠውን መመሪያ ተቀብለው ፶ ድንኳኖች አሰፍተው ለችግረኞቹ ወገኖች እንዲደርስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አስረክበዋል ።

የእያንዳንዱ ድንኳን ዋጋ በገንዘብ ሲተመን ፯፻ ብር ሆኖ የጠቅላላው ድንኳኖች ዋጋ ፴፭ሺ ሲሆን ይኸው የድንኳኖቹ ርዳታ ከዚህ በፊት ከውጭ አብያተ ክርስቲያናትና በጎ አድራጊ ድርጅቶች ለ፲፯ የመጠለያ ጣቢያዎች ከተላኩት የምግብ ዕደላና የችግረኞች መጠያ ድንኳኖች ሌላ ተጨማሪ ርዳታና ለመቀሌ የመጠለያ ጣቢያ የሚውል መሆኑን ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የተሰጠው መግለጫ አመልክቷል ።

ከመምሪያው የተሰጠው መግለጫ እንዳመለከተው በዓመት ውስጥ ፪፻፵ሺህ ችግረኞችን ለመርዳት እንዲቋቋሙ ከታቀዱት ፲፯ ጣቢያዎች ውስጥ ፤

ሀ/ በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባሰል አውራጃ በሀይቅ፣
ለ/ በትግራይ ክፍለ ሀገር ርእሰ ከተማ በመቀሌ ፤
ሐ/ በኤርትራ ክፍለ ሀገር በከረን አውራጃ በሀጋዝ፣
መ/ በጎንደር ክፍለ ሀገር በሌቦ አውራጃ በእብናት ወረዳ የመጠለያ ጣቢያዎቹ በመቋቋምና ሥራቸውን በመጀመር ላይ መሆናቸውን ጨምረው ገልጸዋል ።



## ለበዓለ ትንሣኤ በስ/ ወን/ ሐዋ/ ተልእኮ መምሪያ ስም ለቅዱስነታቸው የተበረከተ መወድስና የአማርኛ ቅኔ

ቦኑ ኃዘን ወትፍሥሕተ ልብ

ለቤተ ክርስቲያን ንግሥት በዕንቌ ባሕርይ ትርሲታ
ወበበትረ መንግሥት ጽኑዕ መለኮታዊ ሢመታ
እስመ ኮነ ወርቀ ተዋሕዶ ዘአጽባዕት ሕልቀታ
ወበእንተ ዝንቱ እስተርእዮታ
ተሀፍረ ጥቀ ዓለም ቀሪ ቦታ ።

ለዓለም ፣
እመሂ ፣ ትትገፈታዕ በገፋዕያን ሠናይታ
ግፉዓን ይትማሠጥዋ ለመንግሥተ ሰማይ በረከታ
ተክለ ሃይማኖት ጳውሎስ ወሊቀ ማእምራን ሥምረታ
ተአምረ ወመንክረ እስመ ይገብሩ በውስቴታ

አማርኛ መወድስ

ስብከተ ወንጌል ፍጹም ፋንታ የሌለው
ግሮ ሠሪ ሆነ በግልጽ ስለሚኖር ሀብታም አገር ግሮ
ወሊቀ ማእምራን ከዚያው ፣ ያኑስኪ ስጠው ዘንድሮ
ለጋዜጠኛ ወለሰባኪ ወለተላላኪ ሳይቀር ሁሉም አብሮ
ያሳፍራልና ለተመልካች
ከመደጀ ሰላም ሰነፍ እንዘ ይነዲ ከቢሮ

ለዓለም ፣
ረሀብሂ ንጉሠ ሥጋ እመ ኢፈትሐ ዶምሮ
ሴዴቅያስ ሕይወትየ ነበረ ተኃፊሮ
ወመቃብሪሁ ይከውን ታሕተ እግረ ማኅረጽ ተድኅሮ
ዕድል ፈንታየ ሴዴቅያስ ሲፈጭ ባቄላ ዓይኑን ታውሮ።
እንኳን ደረሳችሁ አባቶች
የትንሣኤ ሰዎች
እስኪ ላባቶች ትልቅ ወሬ
ከትንሣኤው ፍሬ ።
አባቶች ታዲያ ኸረ አደራ
እንዳትሉኝ ትንሽ አውራ ።
ክርስቶስ ሞትን ጎበኘው
በሀ ሞት ኸረ እያለው ።
ምን ተቀየመ መቃብር
በትንሣኤ ምድር ።
መቃብር ማ ሁሉ ሞልቶ
ጾሙን አደረ ተከፍቶ ።
ሥጋ አልበላም እኔ ስለሚል
የተባረከ በመስቀል ።
የቀረበው ላሕም ለበዓሉ
መስቀልማ ነው ይላሉ ።
በቀያፋ እንጂ አየን
እንደሠዉ በጉን ።
እያደረ እንጂ እየዋለ
መቼ ይቀራል ያመልካለ ።
መትከል ማጽደቁን እየቻለ
በበለስ ዓረግ ተበቀለ ።
ምን ዓረግ ይሆን እባክህ ፤
የተሰቀልከው እንደዚህ ።
ገመድና ዐረግ የት ያውቃሉ
ሁሉን ዐረግነው የሚሉ ።
ማንሣት ብሎት ነው ከመሬት
አዳም በለሷን ያነሣት ።
ሕፃኑ ጠብቷል ስትሉት
አልጠባም እኮ አዳምጡት ።
እኔን ሰው እኮ ብሎኝ
ወልድ አማህ ብለው ነገሩኝ ።
እኔ እኮ መቼ ዝም እላለሁ
ላባቱ ታማኝ እነግራለሁ ።
ከፋፉ ሳይቀር ምን ብሏል
ከፍነው ያለ በመስቀል ።
በመስቀል እንዴት ይከፈን ?
ሳለሁኝ ከፋኝ አስከሬን ።
ሥጋህን በልተው ቢያሙህ
እኔስ በመስቀል አላማህ ።
አይሁድስ ለካ ቄሶች ናቸው
ያስደነግጣል መስቀላቸው ።
ጎኑን ያስወጉት ሰዎች ሁሉ
ደምቀን ሌሊት ታየን አሉ ።
ተከሠተባቸው ይኸው
በመስቀሉ ጉዳቸው ።

ዕንባ አነቀሆይ በመስቀል
ኸረ እስቲ አልቅሰው ዝም አትበል ።
ፋናው ከመሬት ደንግዟል
በመስቀልም ላይ ደም ብዟል ።

ስትስቅ ማን አያት ያች ገረድ
ልትመረምር ስትኼድ ።
ከጴጥሮስ በቀር ማንም
ስቃ ያየ የለም ።
ከእግሩ ጐብጧል ሲዋሽ
ይሁዳ ለመሸሽ ።
ዐርብለት ሲሞት ጌታቸው ,
እንግዲህ አይሁድ ማላቸው ።
የቀኙ መስቀል የጥጦስ
በግራም ያለው የዳርክስ
ከዚህ የክርስቶስ ሲታይ
በመሐል አይደለሞይ ።
የቢታንያው ሆሣዕና
ዓይን እኮ አበራ እንደገና ።
እንደለንጊኖስ ነበር
በዓይን እያዩ መመስከር ።



www.ethiopianorthodox.org

ፀሐይ ሠሌዳህ ጠቁሯል ገና
ወልድ እስኪ ሕሳየን ብራና ።
ቀራንዮ ነሽ የታመንሽ
የክርስቶስን ደመላሽ ።
ስታዘዝ አይታ ለኛ አባቶች
ደግሞ ማርያም አዛኝ አለች ።
እኔስ ከደጋው የማዝነው
በረሀባለሰው ።
ተክለ ሃይማኖት አክሞኝ
እንዲያው ለቤቴ ባዳነኝ ።
ቤተ ክርስቲያን ምን ሳላይ
አጉራየን ፈልግ እንዳትይ ።
ከቶ አይገኝም ልንገርሽ
ያላንቺ ለኔ አጉራሽ ።

ይከፋው ይሆን አበባው
ደጉሞኝ ነበር ብለው ።

ጉዳቱን ከፉው ባያምን
አበባው ደጉመን ።

ጠላት ሲያደባ ማነው ያየው
ይኸው አበባው ሲያደባየው ።
የጳጳሳቱ ቁናቸው
ያምራል እስከላይ ሰፍራቸው ።
ሌሎቹ መቼ ይሰፍሩና
እንደዚህ ባለቁና ።
ቤተ ክርስቲያን ቅጂ ነይ
ታረቂ አላልኩሞይ ።
ቤተ ክርስቲያን ምሪንዳለሽ ?
ፋንታ እንደሌለ ታውቂዋለሽ ።
ተክለ ሃይማኖት ጮማ አርዶልሽ
ልብ የሚደግፍ ሞራል ሰጠሽ ።
አይሰጥሽ ይሆን በመንፈስ
ያለሞ ወራሽ ክርስቶስ ።
ተክለ ሃይማኖት ሁዳዴን
እንዴት ነበረ የሸሹን ።
ታዲያ ፋሲካን በወኔዎ
ቢለዋ ያዙ በጋሻዎ ።
መምህር ክርስቶስ አትርሳን
የትንሣኤ ለት ስታየን
ኑ ተቀኙ በለን ።

መጋቤ ዜና ይቁም ግዛው ።



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org